# የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት

## ስትራቴጂካዊ የትግበራ ዕቅድና መመሪያ በኢትዮጵያ

## 2005



### ራዕይ፥

ሁሉም ሕፃናት ጤናማ የሕይወት ጅማሬ የማግኘት፣ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ የማደግ፣ ተንከባካቢና አነቃቂ አካባቢ የማግኘትና እምቅ ችሎታቸውን በተሟላ ሁኔታ የመዳበር መብታቸው ተረጋግጦ ማየት ነው።

የትምህርት ሚኒስቴር | የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | የሴቶች፣ የሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር

# ማውጫ

## ስትራቴጂካዊ የትግበራ ዕቅድ


ምህፃረ ቃላት ii

1. መግቢያ 1

2. የስትራቴጂው ትኩረት 1

2.1. በቀልዘኢት አስፈላጊነት ላይ የሀገር አቀፍ ቅስቀሳ ጠቀሜታ 1

2.2. የቀልዘኢት የአስተዳደር ሥርዓት 1

2.3. የቀልዘኢት አገልግሎት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት 2

2.4. የቀልዘኢት አገልግሎት ጥራት ማሻሻል 2

2.5. ሕፃናትን ከጥቃትና ከጎጂ ድርጊቶች መጠበቅ 3

3. የኘሮግራሙ ግብና ዓላማዎች 3

4. የተግባር ዕቅድ ዳሰሳ 4

4.1. የኘሮግራም ክፍሎች 4

4.2. የቀልዘኢት አስተዳደር 7

4.3. የትግበራ ሂደት 9

5. ዝርዝር የሥራ ዕቅድ 10

6. የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ 19

# ምህፃረ ቃላት

| | |
|---|---|
| ማአጤመ | ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መልእክተኛ |
| ቀልዘእት | የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት |
| መጐት | መሠረታዊ የጐልማሶች ትምህርት |
| ጤኤኘ | ጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም |
| ጤኤሠ | ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች |
| ትሚ | ትምህርት ሚኒስቴር |
| ጤጥሚ | ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር |
| ገኢ.ልሚ | ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር |
| ወመሀ | ወላጅ መምህር ህብረት |
| ቴሙትሥ | ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና |

# 1. መግቢያ

የቀዳማይ የልጅነት ዘመን፣ ለሕፃናት ስብዕናና ለአቅም ግንባታ ብሎም ለኢኮኖሚያዊና ለማህበራዊ ዕድገት ያለውን ጠቀሜታ በማጤን መንግሥት የሕፃናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ለማሻሻል ጠንክሮ እየሠራ ነው። በመሆኑም በቀዳማይ ልጅነት ሁኔታ ላይ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የፖሊሲ ማዕቀፉን ተግባራዊ ለማድረግ ይህንን ስትራቴጂካዊ የአፈፃፀም ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል። በስትራቴጂካዊ የዕቅድ አፈፃፀም ትግበራ ሂደት የወላጆች ትምህርት፣ ጤናና ቀዳሚ ማነቃቂያ፣ ቅድመ መደበኛ ትምህርትና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ለትምህርት ዝግጁነት የሚውሉ አራት መሠረታዊ ምሰሶዎች አሉት።

# 2. የስትራቴጂው ትኩረቶች

በ1999 ዓ.ም በተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ውጤት መሠረት በርካታ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ግልጽ ሆነዋል። ከነዚህም ውስጥ መሠረታዊ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው።

## 2.1 በቀልዘኢት አስፈላጊነት ላይ የሀገር አቀፍ ቅስቀሳ ጠቀሜታ

መንግሥት እስከ መንደር ድረስ በዘረጋው የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አማካኝነት በሕፃናት ሕይወት ላይ ተጨባጭ መሻሻልን አምጥቷል። ይሁን እንጂ ይህ መሻሻል በቅድመ መደበኛ ትምህርት የተፈለገውን ያህል አይደለም። የቅድመ መደበኛ ትምህርት ግዴታ ያለመሆን ወይንም ከመደበኛው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሥርዓት ጋር የተቀናጀ አለመሆን ችግሩን የበለጠ አጉልቶታል። በዚህም ምክንያት በጣም ብዙ ሕፃናት አንደኛ ክፍልን የሚጀምሩት ያለምንም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተሞክሮ ነው። በመሆኑም የሕፃናት የተሟላ ስብዕና መዳበርና ለትምህርት ዝግጁነት በተመለከተ የወላጆች ግንዛቤ ማዳበር አስፈላጊ ነው።

## 2.2 የቀልዘኢት የአስተዳደር ሥርዓት

በአሁኑ ሰዓት የሕፃናት ኘሮግራሞችን መተግበር በአብዛኛው በተለያዩ መንግሥታዊ ባልሆኑ አጋሮች እጅ ያለ ሲሆን እነዚህ ድርጅቶች ላለፉት ዓመታት የቀልዘኢትን አገልግሎት ለሕፃናት ሲሰጡ ቆይተዋል። አጋሮቹ እንደ የሕፃናት አድን ድርጅት፣ ክርስቲያን የሕፃናት ፈንድ እና ኤስ.ኦ.ኤስ ዓለም አቀፍ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። በተጨማሪም እንደ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን፣ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያንና መድረሳ (በሙስሊሙ ማህበረሰብ የሚቋቋሙ የትምህርት ተቋማት) የመሳሰሉት የእምነት ተቋማት የጀመሩዋቸው ሥራዎች እንዳሉ ግልጽ ነው። ዩኒሴፍና ዩኔስኮም የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን በመንደፍ የሕዝብን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚጠቅሙ መረጃዎችን በማመንጨትና በማሠራጨት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። አገር በቀል መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ውስጥም እንደ አዲስ ዴቨሎኘመንት ቪዥን፣ አበበች ጐበና የሕፃናት መንከባከቢያና ማሳደጊያ ድርጅት፣ሰላም የሕፃናት መንደርና ኮድ ኢትዮጵያ የመሳሰሉት ለሕፃናት አገልግሎት በመስጠት የሚጠቀሱ ናቸው።

ሆኖም የተቀናጀ የመንግሥት ተሳትፎ ያለመኖር የሥራዎቹ መበታተን ከበርካታ ክፍተቶችና ድግግሞሽ ጋር ተዳምሮ በተግባር እንደተፈለገው ሥራ ላይ ውሎ ስኬታማ እንዳይሆን አድርጓል። ስለሆነም የመንግሥት ተሳትፎ መኖር የተበታተኑ ጥረቶችን በማቀናጀት ሰፋ ያለ ትግበራን ለማከናወንና ለማበረታታት ያስችላል። ቀጥተኛ ተጠያቂነት እንዲኖር የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነትና ተግባር በዝርዝር ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ይህም የሕፃናትን መብቶች የማስጠበቅና ሕፃናትን የመንከባከብ ተግባራት በበቂና በተቀናጀ አሠራር እንዲተገበሩ ያደርጋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት የሕፃናትን ዕድገት ተቋማዊ በሆነ መልኩ ለመደገፍና ሕይወታቸውን ለማሻሻል በማለም የፖሊሲ ማዕቀፍ አዘጋጅቷል። ይህም የሕፃናትን ዕድገት ለማሻሻልና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃና ስፋት ለማጠናከር የመንግሥት ቁርጠኝነትን ያመላከተ ተግባር ነው።

## 2.3 የቀልዘአት አገልግሎት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት

በቀልዘአት አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ውሱንነት ምክንያት እስከአሁን ያለው የቅበላና ተሳትፎ መጠን በጣም ዝቅተኛ ነው። በ2001 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቅበላ 4.2% ብቻ የነበረ ሲሆን በ2004 ዓ.ም መደበኛ ባልሆነ መልኩ የሚካሄደው የሕፃን ለሕፃንና የዜሮ ክፍል ተሳታፊዎችን በማካተት ወደ 21.6% ከፍ ብሏል። ። የሕፃናትን ጤናና አመጋገብ ለማሻሻል በጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም በኩል ብዙ ነገር እየተሠራ ይገኛል። ሆኖም ግን የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ውጤታማነት ለመጨመር ቀዳሚ ማነቃቂያና የትምህርት ዝግጁነትን ማጠናከር ጠቃሚ ነው። እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ብክነት ለማሻሻል በጣም ብዙ መሥራት እንደሚያስፈልግ መታወቅ አለበት።

## 2.4 የቀልዘአት አገልግሎት ጥራት ማሻሻል

በ1999 ዓ.ም በተካሄደው የነባራዊ ሁኔታ ትንተና ጥናት ውጤት መሠረት በቀልዘአት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የታዩ ብዙ ችግሮች አሉ። ከነዚህም መካከል ባለሙያዎች ትክክለኛ ሥልጠና አለማግኘታቸው፣ የጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት አለመኖር (ለምሳሌ ብሔራዊ መስፈርትና መመሪያ) ለባህል ተዛማጅነት ያላቸው ተገቢ የሆኑ የመማር ማስተማር ቁሳቁሶች ያለማግኘት፣እንዲሁም መሠረተ ልማትና ሀገር አቀፍ ሥርዓተ ትምህርት በተሟላ መልኩ ያለመተግበር ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እነዚህ ችግሮች ጥራት ያለው የቀልዘአት አገልግሎት በመስጠት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድረዋል። ከዚህም በተጨማሪ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት አለመኖር እና አሁን ያለውን መዋቅር ለማጠናከር የሚጠቅሙ መረጃዎች ውሱንነት የራሳቸውን ድርሻ አበርክተዋል።

ምንም እንኳን ከ4-6 ዓመት ላሉ ሕፃናት ሥርዓተ ትምህርት ቢቀረፅና፣ጥራትን የማረጋገጥና ፈቃድ የመስጠት አሠራር ለማዘጋጀት ቢሞከርም ተገቢ አፈፃፀም እና ውጤታማ ሥርዓት በመዘርጋት ዙሪያ ግን ገና ብዙ መሠራት ያለበት ነው። የሕፃናትን የተሟላ ዕድገት ለማፋጠን የአገልግሎት ጥራት ማሻሻል አሁንም ትኩረት ይፈልጋል።

## 2.5 ሕፃናትን ከጥቃትና ከጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች መጠበቅ

ላለፉት የተወሰኑ ዓመታት የኢትዮጵያ መንግሥት ሕፃናትን የመጠበቅ ፍላጐት እና ቁርጠኝነት መሻሻል አሳይተዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት በሽግግሩ ወቅት በታህሳሥ ወር 1984 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ስምምነትን መቀበሉ አንድ ጥሩ መሠረታዊ ማሳያ ነው። ሆኖም ግን የሕፃናት የልደት ምዝገባን ለማስፋፋትና ሕፃናትን ከጉልበት ብዝበዛ፣ ካለ ዕድሜ ጋብቻና ከመሳሰሉት ጐጂ ባህላዊ ድርጊቶች ለመጠበቅ ብዙ መሥራት ያስፈልጋል።

# 3. የፕሮግራሙ ግብና ዓላማዎች

ከነባራዊ ሁኔታ ትንተና ጥናት የወጡ ጉዳዩችን ከታለሙበት ለማድረስና የብሔራዊ ፖሊሲ ማዕቀፉን ለመተግበር የሚያስችል ዕቅድ ለማዘጋጀት ግልጽ የሆነ ግብና ስትራቴጂካዊ ዓላማዎች ተቀምጠዋል።

### ግብ፣

የዚህ ፕሮግራም ግብ አጋርነትና የዓቅም ግንባታ ሥራዎችን በማጠናከር ሁሉም ሕፃናት (ከቅድመ ወሊድ እስከ ሰባት ዓመት) ጥሩ የሕይወት ጅማሬ እንዲኖራቸው የቀልዘእት አገልግሎት ሥርዓትን ጥራት፣ ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ማሻሻል ነው።

### የፕሮግራሙ ዓላማዎች፣

1. ለቀልዘእት ተያያዥነት ያለው መዋቅር በመዘርጋት በተገቢ የብሔራዊ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች የቀልዘእት ተግባራትን ማካተት፣
2. ለሁሉም ሕፃናት በተለይም ለተዘነጉና ለተጐዱ ጥራት ያለው ተደራሽና ፍትሐዊ የቀልዘእት አገልግሎት መሰጠቱን ማረጋገጥ፣
3. የቀልዘእትን ጥራትና ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አጋዥ ሥርዓቶች መዘርጋት፣ መመሪያዎች ማውጣትና ድጋፍ መስጠት፣
4. ሕፃናትን ከማንኛውም ጥቃትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መጠበቅ እና መከላከል፣
5. ለሕፃናት ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠትና ፕሮግራሙን ለመዘርጋት በባለድርሻ አካላት መካከል አጋርነትና ትብብር ማጠናከር ናቸው።

# 4. የተግባር ዕቅድ ዳሰሳ

## 4.1 የኘሮግራሙ ክፍሎች

የፖሊሲ ማዕቀፉን ለማሳካት የሚረዱ ዋና ዋና ክፍሎች ተብለው የሚታሰቡት አራት መሠረታዊ ምሰሶዎች በብሔራዊ ፖሊሲ ማዕቀፉ ውስጥ ተለይተው ተቀምጠዋል።




*ሥዕል 1፡ አራቱ የቀልዘእት ፖሊሲ ማዕቀፍ ምሰሶዎች*

### 4.1.1 ምሰሶ አንድ፣ የወላጆች ትምህርት

የወላጆች ትምህርት ተከታታይ፣ ቀጣይና የረጅም ጊዜ ተግባር ሆኖ የሚያተኩረውም ሕፃናትን በማሳደግና በማጐልበት በኩል ወላጆች/ተንከባካቢዎች የሚኖራቸውን ተግባርና ኃላፊነት መሠረት ያደረገ ግንዛቤና ክህሎት በማስጨበጥ ላይ ነው። ብዙ ወላጆች በሕፃናት ዕድገት ውስጥ በሚኖራቸው ወሳኝ ሚና ላይ ግንዛቤ ወይም መሠረታዊ የሕፃናት አስተዳደግ ዕውቀትና ክህሎት ስለሚያንሳቸው የወላጆች ትምህርት ይህን ሁኔታ ለመለወጥ ያለመ ነው።

ለዚህም ሲባል ትምህርቱ በተለያዩ መንገዶች ሊሰጥ ይችላል።

- ማዕከልን መሠረት ያደረገና ለቡድን ውይይት የሚመች መድረክ በማዘጋጀት፣
- ቤተሰብን ማዕከል ያደረገ ሆኖ ወላጆች የሚኖራቸው ሚና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ የሚታገዝ ማህበረሰብን የማብቃት ተግባራትን በማከናወን፣
- ወላጆችን መሠረት ያደረጉ፣ መልዕክቶች በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በሕትመትና በመሳሰሉት በማሠራጨት፣
- በጐልማሶች ትምህርት ክፍሎች ውስጥ የወላጆችን ትምህርት በማካተት፣
- ሃይማኖታዊ ተቋሞች ከሃይማኖት መሪዎችና ከተጽዕኖ አሳዳሪ ሰዎች ጋር እንዲሠሩ በማድረግና፣
- የወላጅ መምህር ህብረት /ወመህ/ በአካባቢው ባሉ ት/ቤቶች የወላጆች ትምህርት በሰሚናር መልክ እንዲያካሂድ ማድረግን ያጠቃልላል።

### 4.1.2 ምሰሶ ሁለት፣ ጤናና ቀዳሚ ማነቃቂያ/ ቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት/

ጤናና ቀዳሚ ማነቃቂያ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም አማካይነት የሚሰጥ ይሆናል። የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት ዕድሜ ላሉ ሕፃናት ወላጆች/ተንከባካቢዎች ስለተቀናጀ አገልግሎት፣ የሥነልቦና ማህበራዊ ድጋፍና ስለ ቀዳሚ ማነቃቂያ በሚሰጡዋቸው ሥልጠናዎች መሠረት አሳዳጊዎች በዚህ ስራ ይሳተፋሉ። በተቻለ መጠን የቀልዘአት ጣቢያዎች በአካባቢው የሚገኙ ተቋማት ማለትም የማህበረሰብ ማዕከሎችን የጤና ኬላዎችን፣ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችን፣ የቀልዘአት ጣቢያዎችንና የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

የቀልዘአት ጣቢያዎች ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታል፣ የቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ የዕድገትና ጤና ክትትል፣ የዕድገት ፍላጐቶችን ማሟላት፣ በሽታን መከላከል ተግባራት/ጤና አጠባበቅ ባህሪ ማዳበርን ይጨምራል/፣ ሁሉንም ክትባቶች በወቅቱ ማስጨረስ፣ ተጨማሪ ምግብ በወቅቱ በበቂ ሁኔታ ማስጀመር፣ ስለ የማህበረሰብ ጤና ቀናት አገልግሎቶች ወላጆችን/ተንከባካቢዎችን ማስተማርና አገልግሎቶቹ እንዲሰጡ ማድረግ በወላጅ ትምህርት ይጠቃለላሉ። የማህበረሰብ ጤና ቀናት የምግብ እጥረት ያለባቸውን ሕፃናት መደገፍን ባተኮረ መልኩ ይዘጋጃሉ።

ይህ የዕድሜ ክልል ለሕፃናት የአእምሮ ዕድገት በጣም ወሳኝ እንደመሆኑ መጠን ሕፃናትን በለጋ ዕድሜያቸው የምግብ እጥረት እንዳያጋጥማቸው ማድረግና በዕድገታቸው ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ኘሮግራሙ ጎልማሶች ለሕፃናት የሚያደርጉት እንክብካቤና የጎልማሳና ሕፃን ግንኙነት ጥራት በመጠበቅ ቤተሰብንና ማህበረሰብን መሠረት ያደረገ ቀዳሚ ማነቃቂያ ለማጠናከር ይሠራል።

አገልግሎቱ በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና በማህበረሰብ አቀፍ ጤና መልዕክተኞች ይሰጣል። ምክንያቱም እነዚህ አካላት ተመሳሳይ አገልግሎቶች ለማህበረሰቡ እንደሚያበረክቱ ይታወቃል። ስለዚህ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከሕፃናት ተንከባካቢዎች ጋር በመቀናጀት ሥልጠና ወስደው ህብረተሰቡን በዚህ ዙሪያ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

### 4.1.3 ምሰሶ ሦስት፤ ቅድመ መደበኛ ትምህርት፣

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት (4-7 ዓመት) በተለያዩ አካላት የተቋቋሙና የሚተዳደሩ ተቋማት ሲሆኑ ለሕፃናት ዕድገት ማጎልበቻ ማዕከላት አድርጎ መጠቀም ይቻላል። ማዕከላቱ የተቋቋሙትም፣

- በአካባቢ ማህበረሰብ፣
- በግል ባለሀብቶች፣
- እንደ ዕድር ባሉ የማህበረሰብ ስብስብ፣
- በሙያና በህብረት ሥራ ማህበር፣
- በቤተሰብና በጎረቤት ስብስብ በመሳሰሉት ነው።

እነዚህ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት ከፍተኛ ጥራት ያለው የወላጅ/ተንከባካቢና የሕፃን ግንኙነትን የሚያጠናክሩ ናቸው ተብሎ ይታመናል። ወላጆች በጨዋታ የመማርን አስፈላጊነት በመገንዘብ ልጆቻቸውን በተገቢውና ትክክለኛው ዕድሜ ወደ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል መላክ ይኖርባቸዋል። የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል/ አካባቢ የማያሰጋና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሁም ለሕፃናት ተስማሚና ምቹ መሆን አለበት። ስለ ሕፃናት ዕድገትና በቤት ውስጥ ስለሚያስፈልጋቸው የድጋፍ ዓይነት ለመወያየት የመምህራን/ተንከባካቢዎችና ወላጆች የጋራ መድረክ ያስፈልጋል። በዚህ መሠረት ኘሮግራሙ ሕፃናትን ማዕከል ያደረገና ሁለንተናዊ ዕድገታቸውን የሚያፋጥን ይሆናል። ይህን ለማሳካት ኘሮግራሙ ከማህበረሰቡ ባህል ጋር የተጣጣመና ለዕድገት ተገቢ የሆኑና የቤት ውስጥና ከቤት ውጭ የሚገኙ ቁሳቁሶችንና ተግባራትን ያካተተ መሆን አለበት።

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ኘሮግራም ሕፃናት ለመደበኛ ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያግዙ እንደ ቅድመ ንባብ፣ ጽሕፈት፣ ቆጠራ፣ ሒሳብ የመሳሰሉትን መሠረታዊ ክህሎቶችን በማዳበር ላይ ያተኮረ ነው። ሕፃናት መሠረታዊ የሕይወት ክህሎቶችን ማለትም እጅ መታጠብን እና መልካም የአመጋገብ ባህልን ይማራሉ፤ አቀራረቡም ጨዋታን ማዕከል ባደረገ መልኩ ይቀረፃል። የጤና ሠራተኞች በግንዛቤ ማሳደግ እና ሕፃናትን፣ ወላጆችን እና መምህራንን በማሠልጠን ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል ፕሮግራም ውስጥ የክትባት፣ የዕድገት ክትትልና ጤና አገልግሎቶች ይካተታሉ።

ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በሚኖሩበት አካባቢ፣ ዕድርን መሠረት ያደረጉ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ኘሮግራሞች ይበረታታሉ። ህብረተሰቡ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ኘሮግራምን ከአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች፣ ከመደበኛ ት/ቤት ቅጥር ግቢ ወይም በማንኛውም የህብረተሰብ ጣቢያ እንዲያቋቁም ይፈለጋል።

ለሁሉም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጣቢያዎች ኃላፊነቱን የሚወስደው የትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል። የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የመቆጣጠር፣ ድጋፍ የመስጠት፣ መመሪያዎችንና ደረጃዎችን የማዘጋጀት፣ ሥርዓተ ትምህርት የመቅረጽ፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ሥልጠናዎች የመስጠትና የመጫወቻና የመማሪያ ቁሳቁሶችን የማዘጋጀት ኃላፊነትም አለበት። የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶችም የትምህርት ቁሳቁሶችን የማሟላት ኃላፊነት ይወስዳሉ።

በቀበሌ ደረጃም ጤናን በተመለከተ ኃላፊነቱ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ይሆናል። የሴቶች ማህበራትም የሴቶችን እና የሕፃናትን የነቃ ተሳትፎ ለማጐልበት የማይተካ ሚና ይጫወታሉ። ስለሆነም የሴቶች ማህበራት መስፋፋት የቀልዘአት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል መሠረት ለማስፋፋት ያግዛል።

### 4.1.4 ምሰሶ አራት፣ መደበኛ ባልሆነ መንገድ የትምህርት ዝግጁነት ማጐልበት

በሀገር አቀፍ ደረጃ የቀልዘአት አገልግሎትን መዘርጋት ጊዜ የሚወስድና ጥረት የሚጠይቅ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት በገጠሩና አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ አካባቢ ያሉ ሕፃናትን ለመድረስ መደበኛ ያልሆኑ መንገዶችም ጥቅም ላይ ይውላሉ። ጥቅም ላይ ሊውሉ ከሚችሉ አማራጮች መካከል አንዱ የሆነው ልጅ-ለ-ለልጅ ስትራቴጂ ኘሮግራሙ በተተገበረባቸው ክልሎች ውጤታማ መሆን ጀምሯል።

የልጅ-ለ-ልጅ ስትራቴጂ/አቀራረብ ዋና ቁምነገር በዕድሜ ከፍ ያሉ ሕፃናት (አመቻቾች) ከታናናሽ እህቶቻቸው/ወንድሞቻቸው እና ከጐረቤት ልጆች ጋር በተዋቀረ ጨዋታ መር ተግባራት የሚሳተፉበት ሁኔታ መፍጠር ነው። እነዚህ ተግባራት በአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ሊቃኙ የሚችሉና ከዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር የተጣጣሙ ናቸው። የሕፃናት አመቻቾች ማለትም የ5ኛ ና 6ኛ ክፍል ተማሪዎች በመምህራኖቻቸው የሠለጠኑና የሚመሩ ናቸው። መምህራን እንደ አሠልጣኝና ተቆጣጣሪ ሲሳተፉ ወላጆች ደግሞ እገዛ ያደርጋሉ፤ ሥራውንም ይከታተላሉ። የልጅ-ለ-ልጅ ስትራቴጂ ዋና ዓላማ ለጋ ሕፃናትን ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማዘጋጀት ሲሆን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ውጤታማ የሆነ ወጭ ቆጣቢ ለመደበኛ ትምህርት ዝግጅትን የሚያሻሽል ዘዴ እንደሆነ ይታመንበታል።

## 4.2 የቀልዘአት አስተዳደር

የቀልዘአት ኘሮግራም በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ተግባራዊ ይደረጋል። ሌሎች የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መሥሪያቤቶች በፖሊሲ ማዕቀፉ በተገለፀው መሠረት ተግባርና ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ። እንዲሁም ለስቲሪንግ ኮሚቴው የሂደት ሪፖርት ያቀርባሉ። የስቲሪንግ ኮሚቴ አባላትም የሚከተሉት ናቸው።

- ሚኒስትር ዴኤታዎች
- የቀልዘአት ግብረኃይል ተወካይ
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና
- የልማት አጋሮች ናቸው።

ይህ ኮሚቴ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጭ አካል ሲሆን በተዋረድም እስከ ቀበሌ ደረጃ ይዋቀራል። በየደረጃው የተዋቀረው ስቲሪንግ ኮሚቴ ሕፃናትና ወላጆች የተቀናጀ አገልግሎት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል።

በየደረጃው ያሉ የቀልዘእት ግብረ ኃይል ተግባራት፣

- የቀልዘእት ግብረ ኃይል ለስቲሪንግ ኮሚቴው የቴክኒክ ድጋፍ (የመነሻ ሐሳብ) ይሰጣል።
- ስቲሪንግ ኮሚቴው ግልጽነት ያለው ውሳኔ እንዲሰጥ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- የቀልዘእትን ትግበራ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ያቀናጃል። የግብረ ኃይሉ ተሳታፊ መሥሪያቤቶችን ተጠሪዎች የያዘ ሲሆን የሚመራውም ግልጽ በሆነና ከፍተኛ የትምህርት ዝግጅት ባለው ሰው ይሆናል። የኮሚቴው መሪ ሆኖ የተመደበው በስቲሪንግ ኮሚቴው በተሰጠው የሥራ ድርሻ/ተግባርና ኃላፊነት/መሠረት ይሠራል። የግብረ ኃይሉ ሥራ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሚቋቋሙት የልህቀት ማዕከላት የቴክኒክ እገዛ ያገኛል።

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት ያለውን ኘሮግራም በማቀድ የመሪነት ድርሻ ይኖረዋል። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም አማካኝነት

- የእናቶችና የሕፃናት ጤና፣
- የቤተሰብ ምጣኔ እና ክትባት አገልግሎት፣
- የቀዳሚ ማነቃቂያ አገልግሎት፣
- የምግብና የወጣቶች ጤና ሽፋንን ያካተተ የቤተሰብ ፓኬጅ ተግባራዊ ያደርጋል። በአሁኑ ወቅትም ይህንኑ ተግባር እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን አጠናክሮ ይቀጥልበታል።

ትምህርት ሚኒስቴር፡-

ትምህርት ሚኒስቴር ከ4 እስከ 7 ዓመት የሆናቸውን ሕፃናት በተመለከተ መሪነቱን ይወስዳል።

- ለመምህራን መሠረታዊ የሕፃናት ዕድገት ክትትልና የመጀመሪያ ዕርዳታ አሰጣጥ ክህሎት በተመለከተ ሥልጠና ይሰጣል፣
- የወላጆችን ትምህርት በወላጅ መምህር ህብረት፣ በጐልማሶች ትምህርትና በመገናኛ ብዙኃን በኩል በተቀናጀ መልኩ ያከናውናል፣
- የሕፃናት ጤና አገልግሎት እና የወላጆች ትምህርት በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አማካኝነት እንዲሰጥ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

በሁሉም የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት ጥበቃ ጉዳይ የሴቶች የሕፃናትና የወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርና የፍትህ ሚኒስቴር ኃላፊነት ነው። ሆኖም እነዚህ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ከሌሎች የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ጋር በቅርበት በመሥራት ስለ ሕፃናት መብቶችና ደህንነት ግንዛቤ ይፈጥራል።

በክልል ደረጃ የቀልዘኢት የቴክኒክ ኮሚቴ ከክልል ት/ት ቢሮ፣ ከክልል ጤና ቢሮና ከክልል የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ /ሴህወጉቢ/ተወካዮችና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አጋሮች የተውጣጣ ሆኖ የቀልዘኢትን ተግባራት ያስተባብራል። በወረዳና ቀበሌ ደረጃ የሚኖረው አወቃቀርም ተመሳሳይ መልክ ይኖረዋል።

## 4.3 የትግበራ ሂደት

በሀገር አቀፍ ደረጃ የቀልዘኢት ኘሮግራምን እውን ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ ሃብትን ማፍሰስና የሌሎች ተዋናዮችን የነቃ ተሳትፎ ማቀናጀት ይጠይቃል። የሁሉም ተሳታፊ አካላት በአንድ ዓይነት መንፈስና በተመሳሳይ ግንዛቤ አብሮ መሥራትና ልምድ ለመለዋወጥ ፍቃደኛ መሆን ዘላቂ መሻሻልን ለማረጋገጥ እና አዲስ ነገር ለመፍጠር ወሳኝ ነው። በሚቀጥሉት 4 ና 5 ዓመታት የኘሮግራሙ አቀራረብ ራዕይ፣ ፅንሰ ሐሳብ መሞከርና ማሻሻል፣ የጋራ ግንዛቤ መፍጠርና ማስፋፋት ቁልፍ ነጥቦች ሆነው ይቀጥላሉ። በየደረጃው በተዋናይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች መግባባትና መተባበር የኘሮግራሙ የስኬት ቁልፍ ጉዳይ ሆኖ ስለሚቀጥል ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል።

ኘሮግራሙ ሲጀመር ከህብረተሰብ አቀፍ ቅድመ መደበኛ ትምህርት በስተቀር ሦስቱ ምሰሶዎች በተመረጡ ክልሎች ቢያንስ ለሁለት ዓመት በሙከራ ደረጃ ይተገበራሉ። የህብረተሰብ አቀፍ የቅድመ መደበኛ ትምህርትን አስመልክቶ ግንዛቤው ስላለና በቂ ልምድ የተገኘበት ስለሆነ በሙከራ ወቅት በሌሎች የኘሮግራሙ ምሰሶዎች በተገኘው ጥሩ ልምድ መሠረት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚተገበር ይሆናል። ለዚህም ሲባል በሁለተኛ ዓመት መጨረሻ ግምገማ ይካሄዳል፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በየኘሮግራሙ ተገቢነት፣ ውጤታማነትና ወጪ ቆጣቢነት ላይ አጠቃላይ ወጥ መረጃ ያገኛሉ።

የሙከራ ትግበራውን ለማከናወን በሥራ ላይ ያሉ የጤና ሠራተኞችን እና መምህራንን እንደ ቁልፍ ተዋናዮች መጠቀም ይቻላል። አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ ሰፋ ያለ የቀዳሚ ማነቃቂያ እና የወላጆች ትምህርት ሥልጠና ይወስዳሉ። ይህ መንገድ የልጅ-ለልጅ አቀራረብ ሙከራ ላይ በከፊል ተተግብሯል። የኘሮግራሙን የረጅም ጊዜ ትግበራ ለማገዝ የቅድመ-አገልግሎት ሥልጠና መጀመር ይኖርበታል። ይህም እውን ሊሆን የሚችለው በጤና ኮሌጆችና በመምህራን ትምህርት ተቋማት የቀልዘኢት ትምህርት ክፍል በማቋቋም ነው።

በክትትልና ግምገማ ተግባራት ውጤቶች ላይ በመመሥረት ሀገር አቀፍ የማስፋፋት ኘሮግራም ተቀርፆ ይተገበራል። በሂደትም ሁሉንም የሀገሪቱን ክልሎች ያጠቃልላል።ወጪ ቆጣቢነትንና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ኘሮግራሙ በመደበኛ ሁኔታ ክትትል ይደረግበታል።

## 5. ዝርዝር የሥራ ዕቅድ

| ዓላማ 1. ለቀልዘእት ተስማሚ የአስተዳደር መዋቅር መዘርጋትና ቀልዘእት በሁሉም ተዛማጅ ብሔራዊ ፖሊሲዎች እና ኘሮግራሞች መካተቱን ማረጋገጥ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተግባራት | የሚመለከተው ባለድርሻ | ቁልፍ ውጤቶች | ጊዜ | | | | |
| | | | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 |
| የስቲሪንግ ኮሚቴ ማቋቋም/ማዋቀር/ | ትሚ | • የስቲሪንግ ኮሚቴው የሥራ መመሪያ/መነሻ (ToR) ተዘጋጅቶ ይፀድቃል | x | | | | |
| | | • የስቲሪንግ ኮሚቴው ስብሰባዎች ይካሄዳሉ፤ | x | x | x | x | x |
| የቀልዘእት ክፍል ማቋቋም | የቀልዘእት አሃድ | • ለስቲሪንግ ኮሚቴው አባላት በቀልዘእት ላይ ሥልጠናዎች ይሰጣሉ | x | x | | | |
| | | • ለቀልዘእት ክፍል የሥራ መመሪያ ተዘጋጅቶ ይፀድቃል | | x | | | |
| | | | x | x | | | |
| | | • አስተባባሪ ይመደባል | | x | | | |
| | | • ሌሎች ሠራተኞች ይመደባሉ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ይተገበራል፤ | x | x | x | x | x |
| የቀልዘእትን የፖሊሲ ማዕቀፍ ማሠራጨት | ግብረ ኃይል | • የፖሊሲ ሰነዶች ለክልሎች ይሠራጫሉ | x | | | | |
| | | • የፖሊሲ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በሁሉም ክልሎች ይካሄዳሉ | x | x | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቀልዘኢት ግንዛቤ በማዳበር ገፅታውን ከፍ ማድረግ | የቀልዘኢት ክፍል | • በመላ ሀገሪቱ የቀልዘኢት ሥልጠናዎች ይካሄዳሉ | x | x | | | |
| | | • የቀልዘኢት ስርጭት ስትራቴጂ ይዘጋጃል | | x | x | | |
| | | • የቀልዘኢት ስርጭት (ቁሳቁሶች) | x | x | | | |
| የአአዩ ውስጥ የቀልዘኢት የልህቀት ማዕከል ማቋቋም | አአዩ፣ ግብረ ኃይል | • የቀልዘኢት የልህቀት ማዕከል መመሪያ ተዘጋጅቶ ይፀድቃል | x | | | | |
| | | • የማዕከሉ ዓመታዊ የሥራ እቅድ ተዘጋጅቶ ይፀድቃል፤ | x | x | x | x | x |
| በዩኒቨርስቲዎች፣ በመምህራን ትምህርት ተቋሞችና ጤና ኮሌጆች የቀልዘኢት አሃዶች ማቋቋም | ክልል ትምህርት፣ ጤና ሴቶች ህፃናት ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎች | • ለክልል ቀልዘኢት ጉባኤዎች መመሪያ ይዘጋጃል፤ ይፀድቃል | x | | | | |
| | | • የቀልዘኢት ሥልጠና ይካሄዳል | | x | | | |
| | | • ክልላዊ ስብሰባዎች ይካሄዳሉ | x | x | x | x | x |
| የቀበሌ የቀልዘኢት ትግበራ ኮሚቴ ማቋቋም | ወትጽ/ቤት ወጤጽ/ቤት ወሴሕወጉጽ/ ቤት | • የኮሚቴው መመሪያ ተዘጋጅቶ ይፀድቃል | x | x | | | |
| | | • ለኮሚቴው የቀልዘኢት ሥልጠና በወረዳ ደረጃ ይካሄዳል። | | x | x | | |
| | | • በቀበሌ ደረጃ ስብሰባዎች ይካሄዳሉ | | x | x | x | x |
| | | • በወረዳ ደረጃ የመልካም ልምዶች ልውውጥ ይካሄዳሉ፤ | | | x | x | x |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቀበሌ ማስተባበሪያ መዋቅር ማቋቋም | ቀትሥቦ፣ ቀጤኮ ቀሴጉ | • የኮሚቴው ቢጋር ተዘጋጅቶ ይፀድቃል | x | x | | | |
| | | • በቀበሌ ደረጃ የቀልዘእት የአሠልጣኞች ሥልጠና ይካሄዳል | | x | x | | |
| | | • በቀበሌ ደረጃ ስብሰባዎች ይካሄዳሉ | x | x | x | x | x |
| | | • በቀበሌ ደረጃ የተሠሩ መልካም ተግባራት ላይ የልምድ ልውውጥ ይካሄዳል። | x | x | x | x | x |
| ቀልዘእት በሁሉም መሥሪያ ቤቶች ስትራቴጂካዊ የልማት ዕቅዶች ውስጥ እንዲካተት ማድረግ | ትምህርት ሚኒስቴር፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር | • የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የቀልዘእት ተጠሪዎች ይሰየማሉ | x | | | | |
| | | • የቀልዘእት ተጠሪ ቢጋር ተዘጋጅቶ ይፀድቃል | x | | | | |
| | | • የቀልዘእት ተጠሪዎች ስለ ቀዳማይ ልጅነት ዕድገት ግንዛቤ ያገኛሉ፣ | | x | | | |
| | | • በኘሮግራሙ የትግበራ ሂደት ላይ የግምገማ ስብሰባዎች ይከናወሉ | x | x | x | x | x |

| ዓላማ 2፡ ለሁሉም ሕፃናት (በተለይም ለተዘነጉና ለተጎዱ) ጥራቱ የተጠበቀ ፍትሐዊና ተደራሽ የቀልዘእት አገልግሎት ማረጋገጥ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተግባራት | የሚመለከተው ባለድርሻ | ቁልፍ ውጤቶች | ጊዜ | | | | |
| | | | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 |
| የሕፃናትን ዕድገት መገምገም | ት/ሚ፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ቀጤኮ፣ ቀትሥቦ፣ የቀበሌ ቀልዘእት ትግበራ ኮሚቴ | • የሕፃናት አጠቃላይ ዕድገት መመዘኛዎች ይዘጋጃሉ፣ ይፈተሻሉ፣ ይተገበራሉ፣<br>• የመገምገሚያ መሣሪያዎች በክልል በእያንዳንዱ ጤና ኬላ ተቀናጅተው ይቀርባሉ | x | x | x<br>x | x<br>x | x<br>x |
| ህብረተሰብ አቀፍ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት በመላ ሀገሪቱ የሚከተሉትን በማሟላት ማቋቋም፣<br>• የቤት ውስጥና / ውጭ መጫወቻ ቁሳቁስ<br>• ዝቅተኛ ወጭ የሚጠይቁ የግንባታ ዕቃዎች<br>• የመምህራን ቅድመ መደበኛ ት/ቤቶች ከተቋቋሙ በኋላ የረዳት መምህራን ደመወዝን መትከል | የቀበሌ ቀልዘት ትግበራ ኮሚቴ<br><br>ህብረተሰቡና የግሉ ሴክተር የቀበሌ ቀልዘእት ትግበራ ኮሚቴ | • ማህበረሰብ አቀፍ የቅድመ መደበኛ ትምህርት በእያንዳንዱ ቀበሌ ተግባሩን ይጀምራል | x | x | x | x | x |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወላጆች፣<br>አሳዳጊዎችና<br>ሞግዚቶች ልጆች<br>የማሳደግ ኃላፊነት<br>ያለባቸው ስለሆኑ<br>በቀልዘኢት ትግበራ<br>ወቅት ሚናቸው<br>እንዲጫወቱ<br>ማስቻል | | • ከቅድመ ወሊድ እስከ 3 ዓመት የሚመለከት የወላጆች ትምህርት ማኑዋል ይፈተሻል ይሞከራል። | x | x | x | | |
| | | • የወላጆች ትምህርት ማኑዋል ተዘጋጅቶ ይፈተሻል (ከ4-6 ዓመት)። | | x | x | x | |
| | | • ቀዳሚ ማነቃቂያ በጤና ኤክስቴንሽን የቤተሰብ ፓኬጅ ውስጥ ይካተታል | x | x | | | |
| | | • የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች እና ማህበረሰብ አቀፍ ጤና መልዕክተኞች ስለ ቀልዘኢት ግንዛቤ ያገኛሉ። | x | x | x | x | x |
| | | • በወመህ ስብሰባዎች ላይ የወላጆች ትምህርት ሥልጠና ይሰጣል። | | x | x | x | x |
| | | • ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የወላጆች ትምህርትን አስመልክቶ በክልል የአሰልጣኞች ሥልጠና ይካሄዳል | | x | x | | |
| | | • በማቴሪያል ዝግጅት ላይ በክልል አሠልጣኞች ሥልጠና ይካሄዳል። | | x | x | x | x |
| | | • በጐልማሶች ትምህርት መርሀ ግብር የወላጆች ትምህርት ይካተታል። | | x | x | | |
| | | • የወላጆች ትምህርት መርሀ ግብር በሬዲዮና በቴሌቪዥን ይተላለፋል። | | | x | x | x |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ከ4-7 ዓመት ያሉ ሕፃናት በቅድመ መደበኛ ት/ቤቶች ወይም መደበኛ ባልሆኑ ማዕከላት ምዝገባ መጨመር | የቀበሌ ትግበራ ኮሚቴ | • የቅድመ መደበኛ ትምህርት ያገኙ ልጆች የትምህርት ተሳትፎ ይጨምራል። | x | x | x | x | x |
| የቅድመ ሥራ እና የሥራ ላይ የቀልዘኢት መምህራንና ባለሙያዎች ሥልጠና ማካሄድ | ትሚ፣ ጤጥሚ፣ | • ቀልዘት በጤና ሠራተኞች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ይካተታል | x | x | x | x | |
| | ሴቶች፣ ሕፃናትና የወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር | • የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ሥርዓተ ትምህርት ይዘጋጃል። ይፀድቃል | x | x | x | | |
| | ትሚ፣ | • የቀልዘኢት ሴሚናሮች በጤና ኮሌጆች ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ይሰጣሉ። | x | x | x | | |
| መምህራንን የሚያግዙ ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት፣ | | • ሥርዓተ ትምህርት ተዘጋጅቶ ይፀድቃል | x | x | x | | |
| | | • የቅድመ መደበኛ ትምህርት መመሪያ ይዘጋጃል፣ ይፀድቃል | | x | x | x | |
| በቀልዘኢት አገልግሎት ሥራ የአመራሩን አቅም ማጐልበት | ትሚ፣ ጤጥሚ | • በእያንዳንዱ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋምና የጤና ኮሌጅ በሚቋቋመው የቀልዘኢት ክፍል አማካኝነት አቅሙ የጐለበተ የቀልዘኢት አመራርና ባለሙያ ይኖራል። | x | x | x | x | x |

| ዓላማ 3፥ የቀልዘኢትን ጥራትና የአገልግሎት ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አጋዥ ሥርዓቶች፣ መመሪያዎችና እገዛዎች መስጠት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተግባራት | የሚመለከተው ባለድርሻ | ቁልፍ ውጤቶች | ጊዜ | | | | |
| | | | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 |
| የሁሉንም ቀልዘኢት ሠራተኞች የትምህርት ማስረጃ ወጥነት እንዲኖረው ማድረግ | ት/ሚ፣ ጤጥሚ | • ወጥነት ያለው የቀልዘኢት ሥልጠና የትምህርት ማስረጃ ሥርዓት ይዘጋጃል | x | x | | | |
| በቀልዘኢት ለሠለጠኑ መምህራንና ሞግዚቶች ዕውቅናና ማስረጃ መስጠት | ትሚ | • በሚመለከተው አካል እውቅና ያገኙ መምህራንና ሞግዚቶች ይኖራሉ | x | x | x | x | x |
| የሞግዚቶችና የመምህራን ቁጥጥርና ፍተሻ ማካሄድ | ትሚ፣ ጤጥሚ | • የቀልዘኢት አመልካቾች (ጠቋሚዎች) በትሚ ጤጥሚ ክትትል መሳሪያዎች ውስጥ ይካተታሉ፣ | x | x | x | | |
| ሁሉንም የቀልዘኢት ጣቢያዎችን እና ቅድመ መደበኛ ት/ቤቶችን መቆጣጠርና መገምገም | ትሚ፣ ጤጥሚ ሴሕወጉሚ | • የቀልዘኢት ቁጥጥርና ግምገማ ማዕቀፍ ይዘጋጃል | x | x | x | | |
| | | • የቀልዘኢት ጠቋሚዎች በሁሉም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የቁጥጥር ሥርዓት ይካተታል | x | x | x | | |

| ዓላማ 4፡ ሕፃናትን ከማንኛውም ጥቃትና ጐጂ ድርጊቶች መጠበቅ እና መከላከል | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተግባራት | የሚመለከተው ባለድርሻ | ቁልፍ ውጤቶች | ጊዜ | | | | |
| | | | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 |
| ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ድንጋጌ ማስተዋወቅ | ሴሕወጉሚ | • የግንዛቤ ማዳበሪያ ዓውደጥናቶች ይካሄዳሉ | x | x | x | x | x |
| | | • ለሕፃናት ጥበቃ የሕግ ክፍተቶች ይለያሉ | x | x | | | |
| ሕፃናትን ከማንኛውም ጥቃት ለመጠበቅ የወላጆች እና ሞግዚቶች የግንዛቤ ማዳበር ሥልጠና | ሴህወጉሚ | • የሕፃናት ጥበቃ ግንዛቤ ሥልጠናዎች ይካሄዳሉ፣ የወላጆች እና ሞግዚቶች ግንዛቤም ይዳብራል | x | x | x | x | x |

**ዓላማ 5፥ የአገልግሎት አሰጣጥና መርህ ግብርን ለሕፃናት ለማረጋገጥ አስፈላጊ አጋርነትና ትብብር በሁሉም ባለድርሻ አካላት ማሻሻልና ማጠናከር**

| ተግባራት | የሚመለከተው ባለድርሻ | ቁልፍ ውጤቶች | ጊዜ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 |
| ሁሉን አቀፍ የቀልዘአት መረብ/ኔትወርክ መመሥረትና ማቋቋም | ግብረኃይልና ቀልዘአት ክፍል | • ለቀልዘአት መረብ/ ኔትወርክ መመሪያ ይዘጋጃል | x | x | | | |
| | | • የቀልዘአት መረብ/ኔትወርክ ይዘረጋል | | x | x | | |
| | | • የቀልዘአት መረብ/ኔትወርክ አባላት ስብሰባዎች ይካሄዳል | x | x | x | x | x |
| ከመንግሥት፣ ከለጋሾች ከግብረሰናይ ድርጅቶች እና ከግል ባለሃብቶች ጋር በመሆን ሀብት ማሰባሰብ | ገኢ.ልሚ፣ት/ሚ ጤጥሚ ሴሕወጉሚ | • በቀልዘአት በጀት ጉዳይ ከገኢ.ልሚ ጋር ግኑኝነት ይጠናከራል፤ | x | x | x | x | x |
| | | • ለቀልዘአት በገኢ.ልሚ በኩል በጀት ይደለደላል፣ | x | x | x | x | x |
| | ግብረኃይልና ቀልዘአት ክፍል | • ለተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች ስለ ቀልዘአት የግንዛቤ ማዳበሪያ ተግባራት ይካሄዳሉ | x | x | x | x | x |
| | ግብረኃይልና ቀልዘአት ክፍል | • የገንዘብ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብሮች ይዘጋጃሉ | x | x | x | x | x |

## 6. የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ

| ዓላማ 1፡ ተስማሚ የአስተዳደራዊ መዋቅር መዘርጋት፣ ማቋቋምና የቀልዘኢት የፖሊሲ ሐሳቦች በሁሉም ተዛማጅ ብሔራዊ ፖሊሲዎች እና መርሀ ግብሮች ውስጥ መካተቱን ማረጋገጥ | | |
|---|---|---|
| ተግባራት | የክትትል አመልካቶች/ጠቋሚዎች | የግምገማ አመልካቾች/ ጠቋሚዎች |
| የቀልዘኢት ፖሊሲ ማዕቀፉን ማሠራጨት | • በየክልሉ የፖሊሲ ዶክሜንት ያገኙ ባለሙያዎች ብዛት በመቶኛ፣<br>• በየክልሉ በፖሊሲው የተካሄዱ ሥልጠናዎች ብዛት፣ | |
| የቀልዘኢት ግንዛቤን በማሻሻል ገጽታውን ከፍ ማድረግ | • በያንዳንዱ የመንግሥት ዕርከን የተካሄዱ የቀልዘኢት ሥልጠናዎች ብዛት<br>• የቀልዘኢት የግንኙነት ስትራቴጂ ለማዘጋጀት የተካሄዱ የምክክር ስብሰባዎች ብዛት<br>• በምክክር ስብሰባዎች የሴክተሮች የውክልና መጠን<br>• የቀልዘኢት ግንዛቤ ለማሠራጨት ጥቅም ላይ የዋሉ የመገናኛ ዘዴዎች | • በቀልዘኢት ጠቀሜታ ላይ የሕዝቡ ግንዛቤ የደረሰበት ደረጃ<br>• ሕዝቡ ስለ ቀልዘኢት መረጃ ለማግኘት የተጠቀመባቸው የተለያዩ ዘዴዎች<br>• የህብረተሰቡ በቀልዘኢት ላይ ያለው የግንዛቤና የትግበራ ደረጃ |
| ስቲሪንግ ኮሚቴ ማቋቋም/ ማዋቀር/ | • በስቲሪንግ ኮሚቴ የፀደቀ መመሪያ መኖር<br>• የተካሄዱ ስብሰባዎች በቁጥር<br>• በስቲሪንግ ኮሚቴው ጉባኤ የመሥሪያ ቤቶች ውክልና መጠን<br>• አስተባባሪ ኮሚቴው የተሳተፈባቸው የቀልዘኢት ሥልጠናዎች በቁጥር | • በመንግሥት ውሳኔዎች ውስጥ የስቲሪንግ ኮሚቴው ሐሳቦች መካተታቸው<br>• የቀልዘኢት ጠቀሜታ ግንዛቤ ስፋትና ጥልቀት<br>• የኮሚቴው የመፍትሄ ሐሳቦች በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች መካተት |

| | | |
|---|---|---|
| የቀልዘኦት ክፍል ማቋቋም | • የቀልዘኦት ክፍል ለማቋቋም የተዘጋጀ መመሪያ<br>• አስተባባሪ መምረጥ<br>• በት/ሚ፣ ክልልና ወትጽ/ቤት፣ ቀትሥቦ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጥ የቀልዘኦት ክፍል መኖር | • የተሰጡ አስተያየቶች የስቲሪንግ ኮሚቴውን ውጤት ማመላከታቸው<br>• የቀልዘኦት ክፍል በዓመታዊ መርሐ ግብር ሥራ የመፈጸም ብቃት |
| በአአዩ ውስጥ የቀልዘኦት የልህቀት ማዕከል ማቋቋም | • የፀደቀ የቀልዘኦት የልህቀት ማዕከል መመሪያ መኖር<br>• አመታዊ የሥራ እቅድ መኖር<br>• በሥራ ዕቅድ የተለያዩ ተግባራት መከናወን<br>• በአአዩ ሥራ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የጀመረ የቀልዘኦት ልህቀት ማዕከል መኖር | • የቀልዘኦት የልህቀት ማዕከሉ ተግባራቱን የመፈፀም ብቃት<br>• የሥራ እቅድ ተግባራት የማከናወን ብቃት<br>• የሃብት አመዳደብ ብቃት |
| ክልላዊ የቀልዘኦት የምክክር ጉባኤ መድረክ ማቋቋም | • የፀደቀ የሥራ መመሪያ መኖር<br>• በክልል ደረጃ የተካሄዱ የቀልዘኦት ጉባኤዎች በቁጥር<br>• በቀልዘኦት ጉባኤዎች የተሳታፊዎች ሥብጥር<br>• የጉባኤ ተሳታፊዎች ብዛት | • የመፍትሄ ሐሳቦችን በሁሉም መሥሪያ ቤቶች የማካተት ብቃት<br>• የክልል ጉባኤ የመፍትሄ ሐሳቦች አፈፃፀም በወረዳ ደረጃ<br>• የቀልዘኦት ጠቀሜታ ያለው ግንዛቤ ስፋትና ጥልቀት |

| | | |
|---|---|---|
| የወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ ማቋቋም | • የፀደቀ የሥራ መመሪያ መኖር<br>• በወረዳ ደረጃ የተካሄዱ የቀልዘእት ሥልጠናዎች ብዛት<br>• በቀልዘእት ጉባኤዎች የተሳታፊዎች ስብጥር<br>• የተካሄዱ የወረዳ ማስተባበር ጉባኤዎች ተሳትፎ በቁጥር<br>• በጉባኤ ወቅት የተሳትፎ ሁኔታ | • የቀበሌ ማስተባበሪያ መዋቅር አካታች የመሆን ሁኔታ<br>• የቀልዘእት ጠቀሜታ ግንዛቤ ጥልቀትና ስፋት<br>• የቀበሌ ማስተባበሪያ መዋቅር የህብረተሰቡን አባላት ፍላጐት የማርካት ሁኔታ<br>• የቀልዘእት ተግባራትን ከመጀመርና ከመምራት አኳያ የቀበሌ ማስተባበሪያ መዋቅር ውጤታማነት በተጠቃሚዎችና በአገልግሎት ሰጪዎች እይታ |
| ቀልዘእት በሁሉም መሥሪያ ቤቶች መርሐ ግብሮች እንዲካተት ማድረግ | • የቀልዘእት ተጠሪ ያቋቋሙ በሕፃናት ላይ የሚሰሩ መሥሪያ ቤቶች ብዛት<br>• የሥራ መመሪ ያፀደቁ የቀልዘእት ተጠሪዎች ብዛት<br>• የቀልዘእት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባ ላይ የተሳተፉ የቀልዘእት ተጠራዎች በመቶኛ<br>• በኘሮግራም ትግበራ ላይ የተካሄዱ የማሻሻያ ጉባኤዎች በቁጥር<br>• በክለሳ ጉባኤዎች ላይ የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ውክልና | • በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ተግባራት ውስጥ ቀልዘእት የተካተተበት መጠን<br>• በቀልዘእት ጠቀሜታ የግንዛቤ ዕድገት መጠን<br>• ጉባኤዎች የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የማካተትና የተግባራት ሪፖርት ሁኔታ |

| | | |
|---|---|---|
| የህፃናትን ዕድገት ሁኔታ ፍተሻ | • የሕፃናት ትምህርትና ዕድገት መመዘኛዎች ይዘጋጃሉ፤ ይፈተሻሉ፣ ይተገበራሉ፣<br>• በክልሎች በእያንዳንዱ ጤና ኬላ የክትትልና ግምገማ ክፍል ይቋቋማል፣ | • የሕፃናት ትምህርትና ዕድገት መመዘኛዎች ተገቢነት ሁኔታ<br>• የክትትልና ፍተሻ ክፍል አላማቸውን ተግባራዊ የማድረግ ሁኔታ<br>• በሕፃናት ትምህርትና ዕድገት መመዘኛ (ሕትዕመ) የቁልፍ ባለድርሻዎች (መምህራን፣ጤና ሠራተኞች ወዘተ) ግንዛቤ ሁኔታ |
| **ዓላማ 2፡ ለሁሉም ሕፃናት (በተለይም ለተዘነጉና ለተጎዱ) ጥራቱ የተጠበቀ ፍትሐዊና ተደራሽ የቀልዘእት አገልግሎት ማረጋገጥ** | | |
| ተግባራት | የክትትል አመላካቾች/ጠቋሚዎች | የግምገማ አመልካቾች/ ጠቋሚዎች |
| በመላ አገሪቱ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት ማቋቋም | • ዝቅተኛ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ባላቸው ቀበሌዎች የዕድር አቀፍ ቅድመ መደበኛ ት/ቤቶች ብዛት<br>• በእያንዳንዱ ቀበሌ የተጀመሩ የህብረተሰብ አቀፍ ቅድመ መደበኛ ት/ ቤቶች ብዛት | • የተቋቋሙ የቀልዘእት ጣቢያዎች በመደበኛነት የመስጠት ሁኔታ<br>• የቀልዘእት አገልግሎቶች ለሕፃናት የተደራሽነት ሁኔታ<br>• ት/ቤት የገቡ ሕፃናት ብዛት |

| | | |
|---|---|---|
| ወላጆችና ተንከባካቢዎች እንደ አሳዳጊነታቸው ኃላፊነት መስጠት | • የወላጅ ትምህርት ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ዓመት መመሪያ የተሻሻለና የተሞከረ መኖር፣<br>• የተዘጋጀና የተፈተሸ የቅድመ መደበኛ ተማሪዎች /4-7 ዓመት/ ትምህርት መመሪያ መኖር፣<br>• በጤና ኤክስቴንሽን መርሀግብር የቤተሰብ ፓኬጅ ውስጥ የቀዳሚ ማነቃቂያ መካተት፣<br>• ስለ ቀልዘኢት ግንዛቤ የጨበጡ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች እና የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መልዕክተኞች በመቶኛ<br>• በወመህ ጉባኤዎች የሚሳተፉ ወላጆች ቁጥር<br>• በክልሎች የተካሄዱ የወላጆች ትምህርት የአሠልጣኞች ሥልጠና ብዛት በቁጥር<br>• በየክልሉ የተካሄዱ የቁሳቁስ ዝግጅት የአሠልጣኞች ሥልጠና ዓውደ ጥናቶች ቁጥር<br>• የአሠልጣኞች ሥልጠና ጉባኤዎችን የተከታተሉ ወላጆች ቁጥር<br>• በጐልማሶች ትምህርት ኘሮግራም ውስጥ የወላጆች ትምህርት ይዘት መኖር/መካተት/፣<br>• በቴሌቪዥን እና በሬዲዮ የተላለፉ የወላጆች ትምህርት ኘሮግራሞች ቁጥር | • በት/ኘሮግራሙ ምክንያት የወላጆች ዕውቀት የመጨመር ሁኔታ<br>• በት/ኘሮግራሙ ምክንያት የልጅ የማሳደግ ተግባር የተሻሻለበት ሁኔታ<br>• በት/ቤት በሕፃናት ዕድገት እንቅስቃሴ ላይ የተሳተፉ ወላጆች በመቶኛ<br>• ቋሚ ክትትል ያላቸው ወላጆች በመቶኛ<br>• የቀልዘኢት ኘሮግራም ጠቃሚ ሆኖ ያገኙት ወላጆች በመቶኛ<br>• የወላጆች ትምህርትን በሬዲዮና በቴሌቪዥን የመከታተል ዕድል ያገኙ ወላጆች በመቶኛ |

| | | |
|---|---|---|
| በትክክለኛው ዕድሜ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም የሚመዘገቡ ሕፃናት ቁጥር እንዲጨምር ማስተዋወቅ /4-7 ዓመት/ | • በቀልዘኢት የሚካተቱ ከ4-7ዓመት የሆናቸው ሕፃናት ብዛት | • ተመዝጋቢዎች የቀልዘኢት ልምድ ያላቸው ሕፃናት ጭማሪ በመቶኛ፤<br>• የቀልዘኢት ሕፃናት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ለመግባት ያላቸው ዝግጁነት ፤<br>• በተመዝጋቢዎች መካከል የሴትና ወንድ ሕፃናት ቁጥር የመቀራረብ ስኬት ሁኔታ፤ |
| ለተዘነጉ ሕፃናት አገልግሎት መስጠት | • ሕፃናት ለሕፃናት ኘሮግራም የተገበሩ ክልሎች በቁጥር፣<br>• በሕፃናት ለሕፃናት ኘሮግራም የመሳተፍ ዕድል ያላገኙ ሕፃናት በቁጥር | • የቀልዘኢት አገልግሎት ያገኙ የተጐዱ ሕፃናት በመቶኛ<br>• አገልግሎት ያገኙ ሕፃናት በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ያሳዩት የዝግጁነት ሁኔታ<br>• የወንድና ሴት መመጣጠን ሁኔታ |
| የቅድመና የሥራ ላይ የጤና ባለሙያዎች ሥልጠና ማካሄድ | • በጤና ኮሌጅ ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች (ጤኤሠ) የተሰጠ የቀልዘኢት ሰሚናር ብዛት<br>• በቀልዘኢት ሴሚናር የተሳተፉ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በመቶኛ<br>• ቀልዘኢትን ያካተተ የጤና ባለሞያዎች ሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርት መኖር<br>• የቀልዘኢት/ቅድመ መደበኛ መምህራን ሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርት መኖር<br>• በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቀልዘኢት ሥልጠና መሰጠት | • ቀልዘኢት ግልጽ የሆነላቸው የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መልዕክተኞች በመቶኛ<br>• የጤኤሠና ማአጤመ የቀዳሚ ማነቃቂያ ሐሳቦች በመደበኛ ተግባሮቻቸው ውስጥ ያካተቱበት ሁኔታ<br>• በአአዩ ለቀልዘኢት ትምህርት የተመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት በመቶኛ |

| | | |
|---|---|---|
| የመምህራን አጋዥ ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት | • የተፈተሸና የፀደቀ የቀልዘኢት ሥርዓተ ትምህርት መኖር<br>• የፀደቀ የቀልዘኢት የመምህሩ መመሪያ መኖር<br>• የተዘጋጀ፣ የተፈተሸና የፀደቀ የቀልዘኢት የመፃህፍት ዝግጅት መመሪያ መኖር | • የመማር ማስተማር ተግባራት ሕፃን ተኮር የመሆናቸው ሁኔታ<br>• መርሐ ትምህርቱና አጋዥ ቁሳቁሶች ተገቢ ተግባራት የመምራት መጠን<br>• መምህራን ማኑዋሉ ይዘት ላይ ያላቸው ግንዛቤ እና የመማር ማስተማሪያ ቁሳቁስ ለማዘጋጀት የተጠቀሙበት መጠን |
| የቀልዘኢት አገልግሎቶችን ለመምራት ሀብት ማሰባሰብ | • በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማትና በጤና ኮሌጆች ተደራሽ የሃብት ማዕከል ማቋቋምና ማደራጀት የሚመሩበት መመሪያ ይዘጋጃል፣ይፀድቃል፤<br>• የህብረተሰብ የቀልዘኢት አገልግሎት አመራር መመሪያ ይዘጋጃል፣ይፀድቃል | • ከቀልዘኢት ሠራተኞች እና የቀልዘኢት ተጠቃሚዎች በመቶኛ<br>• የቀልዘኢት ህብረተሰብ አመራር መመሪያ ብቃትና ጠቃሚነት ሁኔታ<br>• የሕፃናት ሁለንተናዊ ዕድገት አገልግሎት ለመስጠት የማዕከሉ በሃብት አደረጃጀት ሁኔታ<br>• በሚመለከታቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የሚመደብ በጀትና አጠቃቀም ዓመታዊ የዕድገት መጠን በመቶኛ |

| ዓላማ 3፡ የቀልዘአትን ጥራትና የአገልግሎት ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አጋዥ ሥርዓቶች፣ መመሪያዎችና እገዛዎች መስጠት | | |
|---|---|---|
| ተግባራት | የክትትል አመላካቾች | የግምገማ አመላካቾች |
| የቀልዘአት መመዘኛና መመሪያዎች ማዘጋጀት | • የመመሪያ አዘጋጅ ቡድን የተውጣጣባቸው መሥሪያ ቤቶች ስብጥር<br>• የፀደቀ የቀልዘአት መመዘኛ እና መመሪያ መኖር | • የመመዘኛዎች እና መመሪያዎች ይዘትና ሽፋን ሁኔታ<br>• የመመዘኛዎች እና መመሪያዎች ተገቢነት |
| የሁሉንም የቀልዘአት ሠራተኞች የምስክር ወረቀት ወጥ ማድረግ | • የምስክር ወረቀቶች አነፃፃሪ ቡድን የመሥሪያ ቤት ውክልና ስብጥር<br>• ለመምህራን ሥልጠና መርሃ ግብር መመሪያዎች መኖር | • በማሠልጠኛ ኮሌጆች አጠቃላይ የመምህራን ሥልጠና መመሪያ የሚገኝበት ሁኔታ |
| በቀልዘአት የመምህራን ሥልጠና ዕውቅና የምስክር ወረቀት መስጠት | • በት/ሚ የቀልዘአት ዕውቅና ሰጭ ክፍል መቋቋም | • ቀልዘአት ሥልጠና እንዲሰጡ ዕውቅና የተሰጣቸው ኮሌጆች በመቶኛ |
| የወላጆች፣ አሳዳጊዎችና ሞግዚቶች ክትትል | • የቀልዘአት አመላካቾች መዘጋጀት፣<br>• ትምህርት ሚኒስቴር የመቆጣጠሪያ መመሪያ ቀልዘአት አመላካቾች መካተት በመቶኛ፣<br>• ለወላጆች፣ ለመምህራን እና ለተንከባካቢዎች የተሰጠ የቁጥጥርና የድጋፍ ጉብኝት በቁጥር | • በእያንዳንዱ ቀበሌ የተከናወነ መደበኛ እና ውጤታማ የቁጥጥር ሁኔታ<br>• የቁጥጥር ድጋፍ ቡድን ከተሳታፊ መሥሪያ ቤቶች አንፃር ያለው ስብጥር |
| በሁሉም የቀልዘአት ጣቢያዎችና ቅድመ መደበኛ ት/ቤት ማካሄድ | • ከመሥሪያ ቤቱ የተውጣጣ የክትትልና የግምገማ ቡድን መቋቋሙ<br>• የቀልዘአት ክትትልና ግምገማ የአሠራር ሥርዓት መኖር፣<br>• በሁሉም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የቀልዘአት የክትትል አመላካቾች መካተት በመቶኛ | • መደበኛ እና ተገቢነት ያላቸው መሥሪያ ቤቶች ያካተተ ክትትል የማድረግ ሁኔታ<br>• የክትትልና ግምገማ ሪፖርት የመርሐ ግብር ትግበራ የመጠቀም ሁኔታ፤ |

| ዓላማ 4፡ ሕፃናትን ከማንኛውም ጥቃትና ጐጂ ድርጊቶች መጠበቅ እና መከላከል | | |
|---|---|---|
| የተመድ የሕፃናት መብቶችን ማስተዋወቅ | • የተከናወኑ የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥልጠናዎች በቁጥር<br>• ለሕፃናት ጥበቃ የሕግ ክፍተቶችን የሚለይ ሪፖርት መኖር | • የሕፃናት ሕግ መኖር<br>• የሕፃናት ሕግ ሁሉ አቀፍ የመሆን ሁኔታ<br>• ጥቃት የደረሰባቸው ሕፃናትን ጉዳዮች የማቅረብ እና የመወሰን ሁኔታ መሻሻል በቁጥር<br>• ስለ የተመድ የሕፃናት መብቶችን ስምምነት የህዝብ ዕውቀትና ግንዛቤ መሻሻል |
| ሕፃናትን ከማንኛውም የመብት ጥሰት በመጠበቅ ዙሪያ የተንከባካቢዎችን እና የሞግዚቶችን ግንዛቤ ማሳደግ | • የተከናወኑ የሕፃናት ጥበቃ ግንዛቤ ሥልጠናና ወርክሾፖች ቁጥር<br>• በሕፃናት ጥበቃ ጉዳዮች የሠለጠኑ የቀልዘኢት ሠራተኞች በመቶኛ | • የቀልዘኢት ሠራተኞች በሥልጠናው ምክንያት ያመጡት አዎንታዊ ለውጥ (በዕውቀት አመለካከት እና ትግበራ ዙሪያ)<br>• የተመዘገቡ የሕፃናት ጥቃቶች በመቶኛ<br>• የሕፃናት ጥቃት ድርጊቶች መቀነስ<br>• የሕፃናት መብቶች ጥሰት አጋጣሚዎች መቀነስ |

| ዓላማ 5፡ ውጤታማ የአገልግሎት አሰጣጥና መርህ ግብርን ለሕፃናት ለማረጋገጥ አስፈላጊ አጋርነትና ትብብር በሁሉም ባለድርሻ አካላት ማሻሻልና ማጠናከር | | |
|---|---|---|
| ብዙ መሥሪያ ቤቶችን ያገናኘ የቀልዘኢት መረብ/ኔትወርክ መዘርጋት | • የተዘጋጀ የቀልዘኢት መረብ መዘርጊያ ስልት<br>• መሥሪያ ቤቶችን ያገናኘ መረብ መኖር የተካሄዱ የቀልዘኢት ጉባኤዎች በቁጥር<br>• በመረቡ አማካይነት የተፈፀሙ ሀገራዊ ጉዳዮች በቁጥር | • የቀልዘኢት መረብ የሥራ ዕቅዱን የተተገበረበት ሁኔታ<br>• የቀልዘኢት መረብ ውጤታማነት፣ቀልጣፋነትና ተገቢነት በተጠቃሚዎችና በአገልግሎት ሰጭዎች እይታ |
| የቀልዘኢት በጀት እቅድ በግብረኃይሉ ማዘጋጀት | • ሃብት የማንቀሳቀስ ዕቅድ ማዘጋጀት እና ማፅደቅ | • የቀልዘኢት ፖሊሲ ማዕቀፍ ወጪ መሸፈን<br>• ለቀልዘኢት ዓመታዊ የበጀት ዕድገት መጠን |
| መንግሥት ከለጋሾች፣ ከመያዶች እና ከግለሰቦች ጋር በመቀናጀት ሃብት ማሰባሰብ | • ለቀዘኢት የበጀት ድልደላ በገኢልማ<br>• ለተለያዩ ለጋሽ ቡድኖች የግንዛቤ ማዳበሪያ ስብሰባዎች መካሄድ<br>• የሃብት ማሰባሰቢያ መርሐ ዕቅድ ማዘጋጀት | • የበጀት ድልደላ በገኢልሚ በቁጥር<br>• ለተለያዩ ለጋሽ ቡድኖች የተዘጋጁ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባዎች በቁጥር<br>• ሃብት ለማሰባሰብ የተዘጋጁ መርሀ ዕቅዶች በቁጥር |
| ለህብረተሰቡ አስተዳዳሪ ቡድኖች በሃብት አመዳደብ ዙሪያ አቅም ግንባታ ሥራዎች ማካሄድ | • የህብረተሰብ ሃብት አስተዳደርና አመዳደብ መመሪያ ማዘጋጀት<br>• በሃብት አመዳደብ ላይ የአቅም ግንባታ ሥራ ማካሄድ | • የህብረተሰብ ሃብት አስተዳደርና አመዳደብ መመሪያ አጠቃቀም ሁኔታ<br>• በአቅም ግንባታ ዙሪያ የተካሄዱ ስብሰባዎች በቁጥር |

# የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት መመሪያ በኢትዮጵያ

2010

# ማውጫ

## የቀልዘእት መመሪያ


| | |
|---|---|
| ምህፃረ ቃላት | 31 |
| **1.** መግቢያ | 32 |
| **2.** አስፈላጊነት | 33 |
| **3.** የመመሪያው ትኩረት | 33 |
| 3.1 ለጋ ሕፃናት (ቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት) | 33 |
| 3.2 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ዕድሜ (4-7 ዓመት) | 34 |
| 3.3 ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት | 35 |
| **4.** የአራቱ ምሰሶዎች መመሪያ | 36 |
| 4.1 የወላጆች ትምህርት መመሪያ | 36 |
| 4.2 የሕፃናት ጤና እና የቀዳሚ ማነቃቂያ መመሪያ | 42 |
| 4.3 የቅድመ መደበኛ ትምህርት መመሪያ | 49 |
| 4.4 መደበኛ ላልሆነ ትምህርት ዝግጁነት መመሪያ | 58 |

# ምህፃረ ቃላት

| | |
|---|---|
| ማአጤመ | ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መልክተኛ |
| ሴሕወጉሚ | ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር |
| ቀልዘእት | ቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት |
| መጎት | መሠረታዊ የጎልማሶች ትምህርት |
| ጤኤፕ | የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም |
| ጤኤሰ | የጤና ኤክስተንሽን ሠራተኞች |
| ትሚ | ትምህርት ሚኒስቴር |
| ጤጥሚ | ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር |
| ወመህ | ወላጅ መምህር ህብረት |
| ቴሙትሥ | ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና |

## 1. መግቢያ

የለጋ ህፃናትን ዕድገትና ደህንነት ለመጠበቅ መንግሥት ቁርጠኛ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል። ትምህርት ለሁሉም እና የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት መንግሥት የቀዳማይ የልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርትን መሠረታዊ ጠቀሜታ ያምንበታል። እነዚህ ፈታኝ ጉዳዮችን ለማሳካት የዘርፍ ፖሊሲዎችን ያቀፈ ለቀዳማይ የልጅነት ዘመን እንክብካቤ እና ትምህርት አጠቃላይ የፖሊሲ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል። በትምህርት ሚኒስቴር፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር /ሴሕወጉሚ/ በጋራ የተዘጋጀው የፖሊሲ ማዕቀፍ ከቅድመ ወሊድ እስከ 7 ዓመት ላሉ ሕፃናት ነው። በዚሁም መሠረት ይህ የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቷል።

ይህ መመሪያ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክበካቤና ትምህርትን (ቀልዘእት) አቅጣጫዎች አስቀምጧል። ይህም የሆነበት ምክንያት የብሔራዊ ቀልዘእት ፖሊሲ ማዕቀፉን፣ የሕፃናት ሕግን (2000 እ.ኤ.አ)፣ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን አንክብካቤና ትምህርት አገልግሎቶችን ለመተግበር ለሁሉም ባለድርሻዎች፣ ለወረዳዎች፣ ለክልል መንግሥታት፣ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ለብዙዮሽና ሁለትዮሽ አጋሮች፣ ለዩኒቨርስቲዎችና የግል ዘርፎች የመመሪያው ጠቀሜታ የጐላ እንደሚሆን ይታመናል።

በመመሪያው ዝግጅት ሂደት የተወሰኑ ችግሮች አጋጥመዋል። ከእነዚህም ውስጥ በዚህ ወቅት በቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ፖሊሲ ማዕቀፍ ምሰሶዎች የሚካተቱ የአገልግሎት ዓይነቶች ለመለየት ያለው ልምድ ዝቅተኛ መሆኑ አንዱ ነው። እንዲሁም አግባብነት ያለው ተሞክሮ በመለዋወጥ ወይም በመስጠት ረገድ የጐረቤት አገሮችም የፖሊሲ ማዕቀፍ አተገባበር ልምድ ውስን መሆኑ ሌላው ችግር ነው። በዚህ ምክንያት ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም በስተቀር የአፈፃፀም ዕቅዱ የሙከራ ጊዜ ይኖረዋል። ከሙከራው በሚገኝ ልምድ ላይ በመመስረት ጥራት ያለው የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት አገልግሎት መስጠትን እውን ማድረግ ይቻላል። ይህ መመሪያ በሂደት የሚገኙ ተጨባጭ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የሚስተካከልና የሚሻሻልም ይሆናል።

አሁን ባለው ግንዛቤ መሠረት በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ የሚቋቋመው የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ፕሮግራም ክፍል አስተባባሪ አካል ሲሆን፣ ትምህርት ሚኒስቴር ደግሞ ጊዜያዊ አስተባባሪ መሥሪያ ቤት ይሆናል። ሌሎች ቁልፍ ሚኒስቴር፣ መሥሪያ ቤቶች አንደ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ያሉ አገልግሎት ሰጭዎች እንደየአግባቡ የማስተባበርና የማስፈጸም ኃላፊነት አለባቸው። ቅድመ ወሊድ እስከ ሰባት ዓመት ያሉ ሕፃናትን ህልውና፣ እንክብካቤና ሁለንተናዊ ዕድገት ለማረጋገጥ በመመሪያው መሠረት ሥራዎችን ማከናወን ወይም መስራት ከሁሉም የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት አገልግሎት ሰጭዎች ይጠበቃል።

## 2. የመመሪያው አስፈላጊነት

መንግሥት የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ እና ሌሎች የዘርፍ ፖሊሲዎች መሠረት በማድረግ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት የፖሊሲ ማዕቀፍና፣ ስትራቴጅካዊ የአፈፃፀም፣ ዕቅድና መመሪያ አዘጋጅቷል። በዚሁም መሠረት የፖሊሲ ማዕቀፉን ለማስፈፀም አራት መሠረታዊ ምሰሶዎች ተለይተዋል። እነዚህም የወላጅ ትምህርት፣ ጤናና ቀዳሚ ማነቃቂያ ፕሮግራም (ቅድመ ወሊድ-3ተ ዓመት)፣ ቅድመ መደበኛ ትምህርት (4-7 ዓመት) እና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ለትምህርት ዝግጅነት ናቸው። መመሪያው የተዘጋጀው ባለድርሻዎች ጥራት ያለው የቀልዘኢት አገልግሎት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማገዝ ነው። የመጨረሻ ግብም ሁሉም ሕፃናት ጤናማ የሕይወት ጅማሬ እንዲኖራቸው፣ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ፣ ተንከባካቢና አነቃቂ አካባቢ ውስጥ የማደግና ዕምቅ ችሎታቸውን የመዳበር መብት ማረጋገጥ ነው።

ሕፃን ተኮር አቀራረብና አገልግሎት አሰጣጥ ለቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት የማዕዘን ድንጋይ ነው። በሕፃን ተኮርና አሣታፊ ትምህርት አማካይነት ለጋ ሕፃናት አካባቢያቸውን እንዲገነዘቡ ወይም እንዲረዱ የሚረዳ ዕውቀት ይገበያሉ። ይህ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ዋና መርህ ይሆናል። አገራዊና ዓለም አቀፍ ምርምሮችና ልምዶች እንደሚያሳዩት ይህን መርህ ማሳካት ቀላል እንዳልሆነ ይታመናል። ስለሆነም ለመምህራንና ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በሕፃን ተኮር ትምህርትና መስተጋብር ሥልጠና መስጠት ቁልፍ ተግባር ነው።

## 3. የመመሪያው ትኩረት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለሕፃናት ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝ የሆኑ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት አገልግሎቶች አሰጣጥ ላይ ትኩረት ይደረጋል። እነዚህንም አገልግሎቶች ለመተግበር የቀልዘኢት ፖሊሲ ማዕቀፍ አራቱ ምሰሶዎች ዋና መሣሪያዎች ናቸው።

### 3.1 ለጋ ሕፃናት (ቅድመ ወሊድ እስከ 3ተ ዓመት)

የሕፃኑ ቀዳማይ ልጅነት ዘመን ዕድገት በቀጣይ ልጅነትንና ጐልማሳነት ዘመን ሕይወቱ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ተፅዕኖ ያሳድርበታል። እናቶች በቅድመ ወሊድ፣ በወሊድ ጊዜና ከወሊድ በኃላ ስለ ሕፃናትና ስለ ራሳቸው የጤና ፕሮግራሞችና ወላጆች ሕፃናትን እንዴት እንደሚንከባከቡ ትኩረት ተሰጥቶ ይማራሉ። በዚህ ወቅት የተለየ ትኩረት የሚሰጠው ስለ ሕፃኑ ጤና፣ አመጋገብና መልካም አያያዝ ነው። ጡት ማጥባት በጣም ወሳኝ ነው፤ ስለዚህ ሕፃናት በተቻለ መጠን ከእናቶቻቸው ጋር ሆነው እንዲያድጉ የሚቻለውን ሁሉ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይገባል።

የሕፃናት የስሜት ህዋሳትን ለማጐልበት በወላጅ/ተንከባካቢና በልጅ መካከል የሚኖረው መልካም መስተጋብርና ትስስር ለዕድገት ወሳኝ ነው። ሕፃናት ድጋፍ ሲደረግላቸው የአካላዊ ቅልጥፍና፣ የቋንቋ፣ የማሰብና የማህበራዊ ክህሎቶቻቸው በፍጥነት ይዳብራሉ።

የለጋ ሕፃናትን ዕድገት ለማፋጠን የሚያስፈልጉ ነገሮች፣

- እስከ 6 ወር የእናት ጡት ብቻ ማጥባት፣
- ከስድስት ወራት በኋላ ከተጨማሪ ምግብ ጋር ቢያንስ እስከ ሁለት ዓመት የእናት ጡት ማጥባት፣
- ከአካላዊ አደጋ መጠበቅ፣
- በቂ ምግብ መስጠትና የጤና አጠባበቅ /እንክብካቤ ማድረግ፣
- ተገቢ የሆኑ ክትባቶችን በወቅቱ እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ሕፃናት ከአዋቂ ጋር የፍቅር ትስስር እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- ለፍላጎታቸው ምላሽ የሚሰጥና ሊረዳቸው የሚችል አዋቂ በአጠገባቸው መኖር፣
- ሁሉንም የስሜት ህዋሳቶቻቸውን በመጠቀም አካባቢያቸውን መገንዘብ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- አካባቢያቸውን እንዲፈትሹ ዕድል መስጠት፣
- ተገቢ የሆነ የቋንቋ ማነቃቂያ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- የአካል እንቅስቃሴ፣ የቋንቋና የአስተሳሰብ ክህሎት እንዲያገኙ ማገዝ፣
- እራስን የመቻል ብቃት እንዲያዳብሩ ዕድል መስጠት፣
- ባህሪያቸውን እንዴት መቆጣጠር እንዳለባቸው እንዲማሩ መርዳት፣
- እራሳቸውን መንከባከብ እንዲጀምሩ መልካም አጋጣሚዎችን መፍጠር፣
- በተለያዩ ቁሳቁሶች እንዲጫወቱ ዕድል መስጠትና የመሳሰሉት ናቸው።

## 3.2 በቅድመ መደበኛ ትምህርት ዕድሜ ላይ ያሉ ሕፃናት (4-7 ዓመት)

የቅድመ መደበኛ ትምህርት የዕድሜ ክልል ለማህበራዊ ግንኙነትና ለትምህርት ዝግጁነት ትልቅ ጠቀሜታ አለው። በዚህ ዕድሜ ሕፃናት ከአቻዎቻቸውና ከተንከባካቢዎቻቸው ጋር ያለው ትስስርም ይሰፋል። ከአራት ዓመት ጀምሮ ላሉ ሕፃናት የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራሞች የሚያተኩሩት በቅድመ መደበኛ ትምህርትና እንክብካቤ ላይ ነው። ጤናና ሥነ-ምግብ ለለጋ ሕፃናት ከሚያስፈልጉ ነገሮች መካከል ናቸው። ይህ የዕድሜ ክልል ወደ መደበኛ ት/ቤትና ወደ ሰፊው ዓለም የመሸጋገሪያ ጊዜ በመሆኑ ድጋፍ መስጠት ይችሉ ዘንድ ወላጆች መበረታታት ያስፈልጋቸዋል። ቤተሰብና ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት አብረው መስራት ለሕፃናት ውጤታማ ዕድገት አስፈላጊ ነው።

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ዕድሜ ክልል ያሉ ሕፃናትን (4-7 ዓመታት) ዕድገት ለማፋጠን የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች፣

ከላይ ከተጠቀሱት አስፈላጊ ጉዳዮች በተጨማሪ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት (4-7 ዓመት) ለተሟላ ዕድገታቸው የሚከተሉትን ይፈልጋሉ።

- የተለያዩ ክህሎቶችን ማለትም የአካላዊ እንቅስቃሴ፣ የቋንቋ፣ የማህበራዊ፣ የስሜታዊ፣ የግንዛቤና የአስተሳሰብ ችሎታን ለማዳበር የሚያስችሉ አገዛዞችና መልካም አጋጣሚዎችን ማግኘት፣
- የተለያዩ ፅንሰ ሐሳቦችን በሚገባ ለመገንዘብና በተሻለ ሁኔታ ለማዳበር የሚያስችሉ ተግባራት ማቀድ፣
- በንግግር፣ ተረት፣ ንባብና መዝሙር የቋንቋ ችሎታን ማበረታታት፣
- መተባበር፣ መረዳዳትንና ያላቸውን ነገር ማካፈልን እንዲማሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- የቅድመ ጽሕፈት፣ ንባብና ስሌት ልምምድን ማበረታታት፣
- መማርን የሚያግዙ ቁሳቁሶች በተግባራዊ ልምምድ ወቅት መጠቀም፣
- በተግባር ለመማር የዳሰሳ ዘዴ መጠቀም፣
- ኃላፊነት እንዲወስዱና መምረጥ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ራስን ለመቆጣጠርና የጀመሯቸውን ሥራዎች ለመፈፀም የሚያስችል ፅናት እንዲያዳብሩ ማበረታታት፣
- ራሳቸውን የማክበር ስሜት እንዲያዳብሩ መርዳት፣
- ራሳቸውን መግለፅ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ፈጠራን ማበረታታትና፣ራሳቸውን መንከባከብ እንዲችሉና በራሳቸው እንዲተማመኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

## 3.3 ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት

አንዳንድ ሕፃናት በወሊድ ጊዜና ከወሊድ በኋላ የተከሰተ አካላዊ ችግር ሊኖራቸው ይችላል። እነዚህ ሕፃናት እንደማንኛውም ሕፃን መብታቸው ሊከበር ይገባል። መብታቸው ከተጠበቀና ለዕድገት አመቺ በሆነ አካባቢ ካደጉ ለህብረተሰቡ በጎ አስተዋጽዖ ያበረክታሉ። ለሕፃናቱ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር የወላጅና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ኃላፊነት ነው። ለሕፃኑ ጥሩ አማራጭ ሲሆንና አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ብቻ ተቋማዊ እንክብካቤ ይሠጣል።

ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሕፃናት ዕድገት ለማፋጠን ከላይ ከተጠቀሱት አስፈላጊ ጉዳዮች በተጨማሪ የሚከተሉትም ያስፈልጋሉ፣

- በጤና ኬላዎች ወይም በሌሎች ቦታዎች እንደ ምክር፣ የምልክት ቋንቋ እና የመሳሰሉት የተሐድሶ አገልግሎቶች መስጠት፣
- ልዩ ፍላጐት ላላቸው ሕፃናት ተስማሚ የሆኑ ቁሳቁሶችና ግብአቶች ማቅረብ፣
- ተስማሚ የሆኑ የቤት ውስጥና የውጭ መገልገያዎች ማሟላት፣
- የቀልዘአት መገልገያዎች ልዩ ፍላጐት ላላቸው ሕፃናት ምቹና ተደራሽ መሆንና፣
- ለሕፃናቱ የሚስማማ ሥርዓተ ትምህርት መቅረፅ ናቸው።

# 4. የአራቱ መሠረታዊ ምሰሶዎች መመሪያ

ይህ ምዕራፍ ስለ አራቱ የቀልዘአት ፖሊሲ ማዕቀፍ መሠረታዊ ምሰሶዎች የአፈፃፀም አቅጣጫ ማብራሪያ ይሰጣል። ሕፃን ተኮር አቀራረብ ሁሉን አቀፍና አጠቃላይ ቀልዘአት ተገቢ በሆነ መንገድ ለመተግበር የጀርባ አጥንት ሆኖ ያገለግላል። በትግበራው ሂደት በተገኙት ልምዶችና ትምህርቶች መሠረት መመሪያው ሊሻሻል ወይም ሊስተካከል ይችላል።

## 4.1 የወላጅ ትምህርት መመሪያ

በኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ የሆነ የወላጅ ትምህርት ልምድ ውስን በመሆኑ ክልሎች መጀመሪያ የሙከራ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳሉ። በተወሰኑ ክልሎች የወላጅ ትምህርት ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት ፕሮግራም ጋር የሚካተት ሲሆን በሌሎች ክልሎች ደግሞ ከልጅ-ለልጅ ፕሮግራም፣ ከጐልማሶች ትምህርት ፕሮግራም፣ ወይም ከጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ጋር ሊካተት ይችላል።

### 4.1.1 የወላጅ ትምህርት ፕሮግራም ሲቀረጽ ታሳቢ የሆኑ ጉዳዮች

- የልጅ አስተዳደግ በትምህርት ሊሻሻል ይችላል፤ ወላጅ ወይም፤ ተንከባካቢ መሆን ከሁኔታዎች ጋር የሚሄድ ተከታታይ የሆነ ማሻሻያና ለውጥ ይፈልጋል።
- ወላጆች እና ተንከባካቢዎች መሠረታዊ ዕውቀትና ክህሎት አላቸው።
- ወላጆች/ተንከባካቢዎች የተለያዩ የመማር ፍላጐቶችና ስልት አላቸው።
- በሕፃናትና ወላጆች/ተንከባካቢዎች ፍላጐቶች ላይ ማተኮር አስፈላጊ ነው።

ወላጆች፣ ተንከባካቢዎች የራሳቸውን ሥልጠና መምራት ይችላሉ። ይህም ማለት ምን መማርና እንዴት መማር እንዳለባቸው በመለየት የራሳቸውን ሥልጠና መምራት ነው።

- ወላጆች/ተንከባካቢዎች ልምዳቸውን እርስ በእርስ መለዋወጥ ያስፈልጋቸዋል፤ ምክንያቱም ትምህርት ተገቢነት የሚኖረው ይዘቱ ከልምዳቸው ጋር ግንኙነት ወይም ቁርኝት እንዲኖረው ሲደረግ ነው።

- ወላጆች/ተንከባካቢዎች እርስ በርስ መተጋገዝ ይችላሉ፤ በዚህ መሠረት ልምዳቸውን በመለዋወጥ ብቃታቸውን የሚያዳብሩበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባል።
- ወላጆች/ተንከባካቢዎች የተማሩትን ተግባር ላይ ማዋል ያስፈልጋቸዋል። ስለሆነም አዲስ ትምህርት ከመማራቸው በፊት ባለፈው የተወያዩባቸው ፅውቀቶችና ክህሎቶችን በመሞከር የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ ማገዝ ያስፈልጋል።

### 4.1.2 በወላጆች ትምህርት የሚካተቱ የህብረተሰብ ክፍሎች

በልጅ አስተዳደግ ፕሮግራም የሚካተቱ የህብረተሰብ ክፍሎች፣

- ከቅድመ ወሊድ እስከ 7 ዓመት ያሉ ሕፃናት ወላጆችና ተንከባካቢዎች ፆታን፣ ማህበራዊ ደረጃን ወይም ዘርን ሳይለይ፣ ለችግር ተጋላጭ ሕፃናት ትኩረት በመስጠት፣
- ሠራተኛ እና ቤት የሚውሉ ወላጆች/ተንከባካቢዎችን ያጠቃልላል።

> ***መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦***
>
> ▶ ከ30-40 ያልበለጡ የቡድን ተሳታፊዎች፣
>
> ▶ የተሳታፊዎች ስምና አድራሻ ምዝገባና ትምህርት ሲጀምሩ የልጆቻቸውን ብዛት እና ዕድሜ ማወቅ፣
>
> ▶ አመቻቹ በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ የተሳታፊዎችን ስም ዝርዝር ይይዛል።

### 4.1.3 የወላጆች ትምህርት ፕሮግራም ይዘት

የወላጆች ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ሲቀረፅ የተለያዩ ዕድሜ ያላቸውን ሕፃናት እና በተለያየ ሁኔታ የሚገኙ ቤተሰቦች ፍላጎት እንዲያሟላና እንዲጣጣም ተደርጎ የሚዘጋጅ ይሆናል። ትምህርቱ የሚያተኩርባቸውም፣

- ሁለንተናዊ የሕፃናት የዕድገት ዘርፎችን፣
- ሁሉን አቀፍ ዕድገትን ለማበረታታት ቀዳሚ ማነቃቂያ፣ የወላጅ ሕፃን መስተጋብር/መግባባት፣ ምግብና አመጋገብ፣ ንፅህናና የታመሙ ሕፃናትን መንከባከብ፣
- ሥርዓተ-ፆታን መሠረት ያደረገ የህፃን ዕድገት ጉዳዮች፣
- ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በተመለከተ፣
- ውጤታማ የልጅ አስተዳደግ ተግባራት፣
- የሕፃንና የአዋቂ ትስስርንና ግንኙነትን ማዳበር፣
- የኤች አይ ቪ/ኤድስን መሠረታዊ ግንዛቤዎች፣
- የአዎንታዊ ሥነ-ምግባር ግንባታ፣
- የሕፃናት መብቶችና ጥበቃን እና የመሣሰሉት ናቸው።

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦**

- ▶ በሁለንተናዊ የሕፃናት ዕድገት ላይ ማተኮር፣
- ▶ የሁለንተናዊ ዕድገት መሠረቶችንና የወላጆች/ተንከባካቢዎች ሚናን ማካተት፣

### 4.1.4 የጊዜ ሠሌዳና የሥልጠና ቦታ

- ዓመቱን በሙሉ የወላጆች መደበኛ ጉባዔዎች ይካሄዳሉ፣ በወር አንድ ጊዜ ለአንድ ሰዓት ያህል በአጠቃላይ በዓመት 12 ስብሰባዎች ይካሄዳሉ።
- ስብሰባዎች ለወላጆች እና ተንከባካቢዎች በሚመች ሰዓት መዘጋጀት አለባቸው፣ እንዲሁም ተሳትፎን ለማረጋገጥ ሌሎች ወላጆችን የሚመለከቱ ጉዳዮችም ግምት ውስጥ ይገባሉ።
- የቤት ጉብኝት ክፍለ ጊዜ ሲወሰን ወላጆችን ካማከሩ በኋላ መሆን አለበት።
- የእናቶች ስብሰባዎች በቡድን መካሄድ አለባቸው ነፍሰ ጡሮች ከ3 ዓመት በታች ሕፃን ያላቸውና ከ4-7 ዓመት ሕፃን ያላቸው ተብለው መከፋፈል አለባቸው።
- የነፍስጡሮች፣ የወላጆችና የተንከባካቢዎች የቡድን ስብሰባ ቦታ ከግማሽ ሰዓት የእግር ጉዞ ያልራቀ መሆን ይኖርበታል።
- የመቀመጫ ወንበሮችና የመማሪያ ማቴሪያሎች መሟላት አለባቸው።
- አመቻቾች ቀድመው ህብረተሰቡን ማጥናትና ተገቢ የሆኑ የመማር ግብአቶች መለየት አለባቸው።

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦**

- ▶ የሥልጠና ክፍሉ ቢያንስ አንድ መስኮትና ንፁህ አየር ማስገቢያ ያለው መሆን ይኖርበታል።
- ▶ ወላጆች/ተንከባካቢዎች ለመመዝገብ ቢያንስ 3 ስብሰባዎችን መሳተፍ አለባቸው።
- ▶ አመቻቹ ተገቢ የሥልጠና ቁሳቁሶችና ግብአቶች መጠቀም ይኖርበታል።

### 4.1.5 የወላጆች ትምህርት የሚሰጥባቸው መንገዶች

የወላጆች ትምህርት የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ሊካሄድ ይችላል፤

- በጤና ኬላዎች ወይም በሌሎች ማህበረሰቡ ለስብሰባ በሚገለገልባቸው ቦታዎች በቡድን ማስተማር፣
- ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መልዕክተኞች ወይም የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በሚያደርጓቸው የቤት ለቤት ጉብኝቶች፣
- በት/ቤቱ በተጠራ የወላጅ መምህር ህብረት /ወመህ/ ጉባኤዎች፣
- ከጐልማሶች ትምህርት ጋር በማቀናጀት፣
- በቀበሌው ከሚካሄዱ የማህበረሰብ ጉባዔዎች ጋር በማቀናጀትና፣
- በመደበኛ የአምልኮ ስብሰባዎች፣ በአብያተክርስቲያናት፣ መስጊዶችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦**

- ፕሮግራሞቹ የሚከናወኑት ወላጆች ሁልጊዜ በሚጐበኟቸው፣ የጤናና የማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍ በሚያገኙባቸውና ምቾት በሚሰማቸው ቦታዎች ነው፡፡
- የወላጆች ትምህርት የሚሰጠው የወላጆች ፍላጐት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

### 4.1.6 የማስተማር ዘዴ

- ሥልጠናው የሚሰጠው ተሣታፊዎች በደንብ ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ መሆን አለበት፡፡ በገጠር አካባቢዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋን መጠቀም በጣም ተመራጭ ነው፡፡
- ጥቅም ላይ የሚውሉ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጐልማሳ ተኮር፣ ውይይትን የሚያበረታቱና ወላጆችና ተንከባካቢዎች ሃሳብ እንዲለዋወጡ ዕድል የሚሰጡና ችግሮችን በጋራ እንዲፈቱ ከእርስ በርስ ዕውቀታቸው ተጠቃሚ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው፡፡
- ስብሰባዎች ማተኮር ያለባቸው ተሣታፊዎችን በዕውቀትና በክህሎት ማጐልበት ላይ ነው፡፡ ትኩረት ሊሰጥ የሚገባው ለአዎንታዊ የባህርይ ለውጥና የተገኘውን ዕውቀት በመተግበር ላይ ነው፡፡
- የማህበረሰቡን ፍላጐት ለመገንዘብ የማህበረሰብ ውይይቶች እና ጭውውቶችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡
- ስሜትን የሚነኩ ጉዳዮች በጥንቃቄ መያዝ ያስፈልጋቸዋል፡፡
- የመማሪያ አካባቢዎች ለተሳታፊዎች ምቹ መሆን አለባቸው፤ አመቻቾችም ተሣታፊዎችን በአክብሮት መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦**

- ሁሉም ተሳታፊዎች የወላጅነት /የተንከባካቢነት ኃላፊነት እንዲሠማቸው ይደረጋል።
- ማንኛውም የፕሮግራሙ ተሳታፊ የዝቅተኝነት ስሜት እንዲያድርበት መደረግ የለበትም።

### 4.1.7 የክፍለ ጊዜ አወቃቀር

የአንድ ስብሰባ የትምህርት አሰጣጥ መግቢያ፣ ይዘትና አቀራረብ፣ መልመጃ/ማጠናከርያና የማጠቃለያ ሃሳብ ይኖሩታል።

- <u>መግቢያ</u>: ስብሰባዎች የሚጀምሩት ስላለፈው ስብሰባና በቤት ውስጥ በሙከራ ስላገኙት ልምድ በአጭሩ አስተያየት በመስጠት ይሆናል። ከዚህ በኋላ የዕለቱ ርዕስ ይተዋወቃል።
- <u>ይዘትና አቀራረብ</u>: ቀጥሎ የሚሆነው ርዕሰ ጉዳዮን የተመለከቱትን እውነታዎች እና ፅንሰ ሀሳቦች ለወላጆች/ተንከባካቢዎች ተግባራዊ ምሣሌዎች በመጠቀም ማቅረብ ነው። እንደዚህ አይነት አቀራረብ ወላጆች ብዙ እንደሚያውቁና በትክክለኛ አቅጣጫ ላይ እንዳሉ የሚያሳያቸው ይሆናል። በዚህ ጊዜ ወላጆች ብዙ ማወቅ እንደሚያስፈልጋቸው እና ስለ ልጅ አስተዳደግ ተጨማሪ ዕውቀትና ክህሎት ማግኘት እንደሚቻል ይረዳሉ።
- <u>አዲስ ባህርይና ክህሎት ለመማር የሚቀርቡ መልመጃዎች</u>: በጣም አስፈላጊው ክፍል ቡድኑ የተስማማባቸውን አዳዲስ ባህርያትንና ክህሎት በቤት መተግበር መጀመር ነው። እዚህ ላይ አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ መረጃዎችን በስብሰባው ርዕስ ላይ መስጠት ይቻላል። ይሁን እንጂ ዋናው ነገር ተግባራዊ ልምምድ ነው። አሠልጣኞች በወላጅ ትምህርት ጥራዝ ላይ ከተገለፁ የተለያዩ መልመጃዎችና ዘዴዎች ውስጥ መምረጥ ይችላሉ።
- <u>የመዝጊያ ሃሣብ</u>: በውይይቱ በተነሱት ሐሳቦች ላይ ተጨማሪ አስተያየት በመስጠት ክፍለ ጊዜውን ማጠቃለል ያስፈልጋል።

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦**

- የትምህርቱን ሐሳቦችና እውነታዎች የወላጅ/ተንከባካቢዎች ልምድ በሚያንፀባርቅ መልኩ ተጨባጭ ምሳሌዎችን በመጠቀም ማቅረብ እና መወያየት።
- ወላጆች/ተንከባካቢዎች ርዕሰ ጉዳዩን በተመለከተ አዲስ መረጃ ይሰጣቸውና አዲስ ዕውቀት ያገኛሉ።

#### 4.1.8 የአመቻቾች አመራረጥ

- አመቻቾች የልጆች አስተዳደግ ሥልጠና የወሰዱ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች እና የቅድመ መደበኛ መምህራን ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም እንደየሁኔታው የጤና ኤክስቴንሽን ሞዴል ቤተሠቦች፣ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መልዕክተኞች እና ሌሎች ሥልጠናውን የወሰዱ በአመቻችነት ሊመረጡ ይችላሉ።
- ለእያንዳንዱ ሙከራ ጣቢያ ሁለት አሠልጣኞች ይመረጣሉ፤ አንዱ/ዷ የጤና ሌላው/ዋ ደግሞ የትምህርት ሥልጠና ያላቸው ይሆናሉ።
- አመቻቾች ስለቀዳማይ ልጅነት ዕድገት በአሠልጣኞቸ ሥልጠና ፕሮግራም፣ በሴሚናር ወይም በመምህራን ሥልጠና ፕሮግራም የሠለጠኑ ይሆናሉ።
- የሚመረጡ አመቻቾች ሁኔታዎችን የሚገነዘቡ፣ ትዕግሥት ያላቸውና ስለ ልጅ አስተዳደግ ተገቢው ግንዛቤ ያላቸው ይሆናሉ።
- አመቻቾች ስለህብረተሰቡ ወግና ባህል በቂ ዕውቀትና ክብር ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

***መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦***

- ▶ ለአንድ የሠልጣኝ ቡድን አንድ አሠልጣኝና ረዳት ያስፈልጋል።
- ▶ አሠልጣኞች የወላጆችን/ተንከባካቢዎችን ቋንቋ የመናገር ችሎታ ያላቸው ይሆናሉ።
- ▶ አሠልጣኞች ስለ ማህበረሰቡ ባህል የሚያውቁ መሆን አለባቸው።

#### 4.1.9 የአመቻቾች የአቅም ግንባታ

የወላጆች ትምህርት ፕሮግራም አመቻቾች አቅም በሚከተሉት መንገዶች ሊገነባ ይችላል።

- የአሠልጣኞች ሥልጠና ከጤጥሚ፣ ከትሚ፣ ከሴሕወጉሚ እና ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር ለሁለት ሳምንት ይሰጣል፣
- ለወረዳ ጤና ጥበቃ ሠራተኞች በሚካሄዱ ሴሚናሮች ይሠጣል፣
- የመምህራን ትምህርት ተቋማት እና የጤና ኮሌጆች ለወላጅ የሚሰጥ የሕፃናት አስተዳደግ ትምህርት በሥርዓተ ትምህርታቸው ውስጥ ያካትታሉ።

***መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦***

- ▶ አመቻቾች በጐልማሶች ትምህርት ወይም በጐልማሶች መሠረተ ትምህርት ማስተማር ልምድ ያላቸው ይሆናሉ፤
- ▶ 8ኛ ክፍልና ከዚያ በላይ የሆኑና አመቻች ለመሆን ፍላጐት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል።

### 4.1.10 የፕሮግራም ውጤታማነት ክትትል

- የክትትል ዝርዝር ነጥቦች መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።
- በሁለንተናዊ የሕፃናት ዕድገት የወላጆች ሚናና ኃላፊነትን በተመለከተ ክትትል መደረግ አለበት።
- ወላጆችን/ተንከባካቢዎችን የወላጅነት ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ስለመሆናቸው መደበኛ ባልሆነ መልኩ ምልከታ ማድረግ።
- የፕሮግራሙን ውጤታማነት፣ ያስገኘው ለውጥና ወጪ ቆጣቢነቱን ለመፈተሽ ከባለድርሻዎች ግብረ-መልስ ማግኘት።

> ***መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦***
>
> ▶ በስብሰባ መገኘትን መከታተል።
>
> ▶ ወላጆች ስብሰባ የተሣተፉበትን ወይም ያልተሣተፉበትን ምክንያት መለየት።

## 4.2 የሕፃናት ጤናና የቀዳሚ ማነቃቂያ መመሪያ (ቅድመ ወሊድ-3+ዓመት)

አሁን ያለው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት ላሉ ሁሉም ሕፃናትና ለወላጆች/ተንከባካቢዎች የተቀናጀ አገልግሎት ይሠጣል። የቀዳሚ ዕድገት ማነቃቂያ ፕሮግራምም በአገልግሎቱ ውስጥ ይጠቃለላል። ይህ አገልግሎት በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና በማሕበረሰብ አቀፍ ጤና መልእክተኞች በሚሰጥ የቤተሰብ ጤና ፓኬጅ ውስጥ የተካተተ ሲሆን፣ በቤት ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ ሊሰጥ ይችላል። የቅድመ ወሊድ አስከ 3+ ዓመት ጤናና ቀዳሚ ማነቃቂያ መመሪያ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ውስጥ የተካተተ ነው።

### 4.2.1 ጤናና ቀዳሚ ማነቃቂያ ትምህርት የሚያተኩርባቸው ክፍሎች

የጤናና ቀዳሚ ማነቃቂያ ፕሮግራም የሚያተኩረው፦

- ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት የዕድሜ ክልል ያሉ ሕፃናት በሙሉ፣
- የሕፃናቱን ወላጆች /ተንከባካቢዎች፣ ፆታ፣ ዘር፣ ማህበራዊ ደረጃ ሳይለይ በተለይ ለችግር ተጋላጭ ለሆኑት ሕፃናት ልዩ ትኩረት በመስጠት ሁሉንም የማህበረሰቡን አባላት ያካተተ ይሆናል።

> ***መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦***
>
> ▶ ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት ያሉ ሁሉም ሕፃናትና ወላጆቻቸውን/ተንከባካቢዎቻቸውን ማካተት።

### 4.2.2 አገልገሎት የሚሰጥባቸው ቦታዎች

ይህ አገልግሎት ከሚከተሉት ቦታዎች ማንኛውንም በመጠቀም ይሠጣል።

- በጤና ኬላዎች፣
- በማህበረሰብ ጣቢዎች ወይም መሰብሰቢያ ቦታዎች፣
- በመኖሪያ ቤቶች፣
- በሞዴል ቤተሰቦች መኖሪያ ቤቶችና በትምህርት ቤቶች ወዘተ.

> ***መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦***
>
> ▶ በእያንዳንዱ መንደር የጤና ማበልፀግ አገልግሎት ይኖራል።

### 4.2.3 ጤና ኬላ እና ሠራተኞች

- የጤና ኬላው መሠረታዊ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መመዘኛዎችን ማሟላት አለበት።
- ሁለት የሠለጠኑ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በጤና ኬላው ይኖራሉ። ጤና ኬላው በየቀኑ አገልግሎት እንዲሰጥ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።
- በጤና ኤክስቴሽን ፕሮግራሞች ትግበራ መመሪያ መሠረት የተመረጡና በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ ስር የሚሠሩ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መልዕክተኞች በየመንደሩ ይኖራሉ።
- የህክምና መገልገያ ቁሳቁሶች፣ መድኃኒቶች፣ የሥራ መመሪያዎች እንዲሁም የቢሮ ዕቃዎች መኖር አለባቸው።
- የጤና ኬላው በቀላሉ እንዲለይ በግልፅ ምልክት ሊደረግበት ይገባል።
- አካባቢው ለእናቶች እና ሕፃናት አካላዊና ስሜታዊ ሁኔታዎች ምቹ ቦታ መሆን አለበት።
- የአካባቢው ንፅህናና ለሕፃናት ምቹ መሆኑ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፤ ቦታው ከብክለትና ከቆሻሻ ነፃ የሆነ መሆን አለበት።
- መሠረታዊ የንፅህና ቁሳቁሶች እጅ ለመታጠብ ከሚያገለግል ውኃ ጋር መኖር አለባቸው።
- ክፍሉ በቂ አየር የሚንሸራሸርበት መሆን አለበት።

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦**

- የጤና ኬላው ተገንብቶ በበቂ ሁኔታ የተደራጀና የተሟላ መሆን፣
- መሠረታዊ የንፅህና መገልገያ፣ ንፁህ የመጠጥ ውኃ እና እጅ ለመታጠብ የሚያመቹ ቁሳቁሶች መኖር፣
- ቢያንስ አንድ የሠለጠነ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ መኖር፣
- ጤና ኬላው መሠረታዊ የጤና አገልግሎቶችን ለመስጠት መቻል ናቸው።

### 4.2.4 የጤና እክስቴንሽን ሠራተኞች ተግባራት (ጤኤሠ)

በጤና ኬላዎች የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በመመሪያው መሠረት ደረጃውን የጠበቀ የቅድመ ወሊድ ክትትል፣ ማዋለድ፣ ክትባት፣ የሕፃናት ዕድገትና ጤና ክትትል፣ ስለ ሥነ ምግብ ማማከር፣ የቤተሰብ ምጣኔና መሠረታዊ የሕክምና አገልግሎቶች ለማህበረሰቡ ይሠጣሉ።

ጤና ኤክስቴሽን ሠራተኞች በጤና ኤክስቴሽን ፕሮግራም የትግበራ መመሪያ መሠረት ቤተሰቦችን በቀልዘእት ያስተምራሉ፣ ያሠለጥናሉ። የእነሱ ኃላፊነት በቀልዘእት ዙሪያ የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

- ሞዴል ሊሆኑ የሚችሉ ቤተሰቦችን እና የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መልዕክተኞችን መለየት፣ ማሠልጠንና ድጋፍ መስጠት።
- በማህበረሰቡ ውስጥ የሞዴል ቤተሰቦችን ተቀባይነትና ተዓማኒነት ማረጋገጥ።
- በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ መሠረት ሞዴል ቤተሰቦች አርኣያ እየሆኑ መምጣታቸውን ማረጋገጥ።
- ከማአጤመ ጋር ሁሉንም ማሕበረሰብ ከዕቅዱ እስከ ግምገማው ማሳተፍና ጤናን የሚመለከቱ መረጃዎችን ማሳወቅ።
- በሴቶችና ወጣቶች ማህበራት፤ በት/ቤቶች እና እንደ ዕድር፣ ማህበር፣ ዕቁብ ባሉ ባህላዊ ማህበራት ማህበረሰቡ ገንዘብና ጥሬ ዕቃ በማቅረብና የጉልበት ዕገዛ በማድረግ እንዲሳተፍ ማደራጀትና ማስተባበር።

### 4.2.5 የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መልዕክተኞች /ሞዴል ቤተሰቦች/ ተግባራት

የቤተሰብ ጤና ፓኬጆችን በመተግበር ሂደት የሕፃናት ዕድገትና ጤና ክትትል፣ በሽታ መከላከል፣ የቤት አያያዝ፣ እንክብካቤ መሻትና ቀዳሚ ማነቃቂያ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መልዕክተኞች የሚያከናውኗቸው ተግባራት ይሆናሉ። እነሱ ሊያበረክቷቸው ወይም ሊሠሯቸው የሚገቡ ቁልፍ የቀልዘእት ልምዶችና ተግባራትም የሚከተሉት ናቸው።

#### 4.2.5.1 ዕድገትን ማበልፀግ

1. ሕፃን እንደተወለደ ሕፃኑና እናቱን አካል ለአካል ማነካካት፣ በአንድ ሰዓት ውስጥ ጡት ማጥባት እና ሕፃኑ እንገሩን እንዲጠባው ማድረግ፣
2. ለስድስት ወራት ሕፃናትን የእናት ጡት ብቻ እንዲጠቡና ለሁለት ዓመታት ወይም ከዚያ በላይ ጡት መጥባት እንዲቀጥሉ ማድረግ፣
3. ተጨማሪ ምግብ ከስድስት ወር በኋላ መጀመርና ጡት መጥባት ለሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ እንዲቀጥል ማድረግ፣
4. ሕፃናት በቂ የሆነ ቫይታሚን 'ኤ' ና 'ዲ'፣ አዮዲንና ብረት ያለባቸው ምግቦችወይም የፀሐይ ብርሃን ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣
5. የሚያነቃቃ አካባቢ በመፍጠርና የሕፃኑን ፍላጐት በማርካት የአዕምሮ እና የማህበራዊ ዕድገቱን ማፋጠን ናቸው።

#### 4.2.5.2 በሽታን መከላከል

1. ሕፃናትን ካፀዳዱና ዓይነምድሩን ካስወገዱ በኃላ፣ ከመፀዳጃ ቤት መልስ፣ ምግብን ከማዘጋጀትና ሕፃናትን ከመመገብ በፊት እጅን መታጠብ ያስፈልጋል፣
2. በየቀኑ ፊት መታጠብን ማስተማር፣
3. በኬሚካል የተነከረ የመኝታ አጐበር በመጠቀምና የወባ ትንኝን መራቢያ በማጥፋት እርምጃ መውሰድ፣
4. የሕፃናት ጥቃት በተመለከተ በወቅቱ ማሳወቅ፣ መከላከል እና ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፣
5. ኤች አይቪ ኤድስን መከላከል፣ በኤድስ ወላጆቻቸውን ላጡና ለታመሙ እንክብካቤና ድጋፍ በተመለከተ ተገቢነት ያለው ጠባይና ልምድ ማበረታታት፣
6. ንፁህ ውኃ መጠቀምን ማበረታታት፣

#### 4.2.5.3 የሕፃናት የቤት ውስጥ አያያዝ

1. ሕፃናት በሚታመሙበት ጊዜ ተገቢውን ምግብና ብዙ ፈሳሽ፣ የእናት ጡትን ጨምሮ መስጠት፣
2. ለታመሙ ሕፃናት ተገቢውን የቤት ሕክምና መስጠት፣
3. የሕፃናትን ጉዳቶች መከላከልና በተገቢው መንገድ መያዝ፣
4. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ማስወገድ /የሴትልጅ ግርዛት፣ እንጥል መቁረጥ፣ ጉሮሮ ማስጧጠጥ፣ ወዘተ/

#### 4.2.5.4 የሕክምና እንክብካቤ መሻት

1. በጊዜ ሰሌዳው መሠረት ሕፃናት ሁሉም ዓይነት ክትባቶችና የዕድገትና ጤና ክትትል እንዲያገኙ ማድረግ፣
2. የታመመው ሕፃን ተጨማሪ ሕክምና እንደሚያስፈልገው ከታወቀ ወዲያውኑ በሠለጠነ ባለሙያ ተገቢ ሕክምና እንዲያገኝ ማድረግ፣
3. ስለ መድኃኒት አጠቃቀም፣ ክትትልና ወደ ተሻለ ሕክምና መሄድ የጤና ሠራተኞችን ምክር መተግበር፣
4. ነፍሰ ጡር ሴቶች የቅድመ ወሊድ ክትትል ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤
5. የሥነ ተዋልዶ ጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ ሴቶችንም ወንዶችንም ማበረታታት፤ ነፍሰ ጡር እናቶች በጤና ተቋም እንዲወልዱ ማድረግ።

#### 4.2.5.5 የቀዳሚ ማነቃቂያ አገልግሎት

1. ከሕፃኑ ጋር ጥሩ ትስስር መፍጠር፤
2. ወላጆች/ተንከባካቢዎች የሕፃኑን ምልክቶች መረዳትና መልስ መስጠታቸውን ማረጋገጥ፤
3. ሕፃኑ የሚያየው፣ የሚነካው፣ የሚሰማው፣ የሚያሸተውና የሚቀምሰው ነገር ማቅረብ፤
4. ህፃኑ አካባቢውን ሊፈትሽ የሚችልበትን ዕድል ማመቻቸት፤
5. በተረት፣ በግጥም፣ በመዝሙርና በመሳሰሉት መንገዶች የቋንቋ ዕድገትን ማነቃቃት፤
6. አዳዲስ የአካል እንቅስቃሴ፣ የቋንቋ እና የአስተሳሰብ ክህሎቶች እንዲያዳብሩ ሕፃናትን ማገዝ፤
7. ራስን መቻል ማበረታታት፤
8. ሕፃኑ እንዴት ባህሪውን መቆጣጠር እንዳለበት እንዲማር መርዳት፤
9. እራሳቸውን መንከባከብ እንዲማሩ ለሕፃናት መልካም አጋጣሚ መፍጠር፤
10. ሕፃናት በተለያዩ ቁሳቁሶች እንዲጫወቱ ዕድሉን መስጠት።

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፡-**

- ሁሉም ነፍሰጡር እናቶች ከወሊድ በፊትና ድህረ ወሊድ በሠለጠነ ባለሙያ ክትትልና አገልግሎት ማግኘት አለባቸው።
- ሁሉም ወላጆችና አሳዳጊዎች ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ትምህርት ማግኘት አለባቸው።
- እያንዳንዱ ወላጅ/ተንከባካቢ በአንድ ዓመት ውስጥ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ስለ ቀልዘእት የማህበረሰብ አቀፍ ትምህርት ማግኘት አለበት።
- ተንከባካቢዎች የማህበረሰብ አቀፍ የሕፃናት እንክብካቤ ፕሮግራም ስለሕፃናት ማነቃቂያ ትምህርት መከታተል አለባቸው።
- ተንከባካቢዎችና እና የቤተሰብ አባላት ስለ ቀዳሚ ማነቃቂያ አገልግሎት እና ተግባራት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።
- ቤተሰብ እና የጤና ዘርፍ ችግር/ጉዳት ያለባቸውን ሕፃናት ቀድሞ የመለየት ሁኔታን ማጠናከር።
- አዲስ የተወለዱ ሕፃናትን፣ እናቶችንና የሕፃናት እንክብካቤ ፕሮግራም ላይ የሚሠሩ አጋሮችን ቁልፍ የሕፃናት እንክብካቤና ማነቃቂያ ተግባራት ማቀናጀት።

### 4.2.6 *መሠረታዊ የጤና እንክብካቤና ማነቃቂያን የማመቻቸት ዘዴዎች*

በሕፃናት እንክብካቤ አገልግሎትና ቀዳሚ ማነቃቂያ ቁልፍ የቤትና የህብረተሰብ ተሞክሮዎች ዕውቀትና ክህሎት በሚከተለው መልክ መቅረብ ይችላል።

- ቀዳሚ ማነቃቂያና የጤና እንክብካቤን በተመለከተ ወላጆች የቤተሰብና የማህበረሰብ ተሞክሮዎች፣ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ በቋንቋቸው ማስተማር ያስፈልጋል።
- ጥቅም ላይ ሊወሉ የሚችሉ ዘዴዎች የማህበረሰብ ውይይትና ጭውውት፣ አንድ ለአንድ ወይም የቡድን የሐሳብ ልውውጥ፣ የልምድ ልውውጥ፣ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ከማአጤመ/ሞዴል ቤተሰቦች ጋር አብሮ በመሥራት በእነሱ በኩል ቁልፍ መልዕክቶችን ለሁሉም ማህበረሰብ ማሰራጨት ይመረጣል።
- ለግለሰቦችና ቡድኖች በማህበረሰብ ውስጥ ምቹ የመማሪያ አካባቢ መኖር አለበት።

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፡-**

- ሁሉም እናቶች እና ተንከባካቢዎች ለሕፃናት እንክብካቤ እና ማነቃቂያ ብቃት ይኖራቸዋል።
- ሁሉም ተሳታፊዎች መሠረታዊ የጤና ማመቻቸት ስብሰባዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ይሳተፋሉ።

### 4.2.7 የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች/ባለሙያዎች መረጣ

በአርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩና በከተማ የሚሠሩ ጤና ሠራተኞች የሚመረጡት በጤጥሚ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ትግበራ መመሪያ መሠረት ነው።

### 4.2.8 ለጤናና ቀዳሚ ማነቃቂያ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መልዕክተኞች መረጣ

የሕፃናት እንክብካቤ እና ማነቃቂያ ፕሮግራም በማበረሰብ አቀፍ የጤና መልዕክተኞች ወይም በመንደሮች በሚገኙ ሞዴል ቤተሰብ በአጠቃላይ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ትግበራ ሥትራቴጂ መሠረት ይስፋፋል።

### 4.2.9 አቅም ግንባታ

የማህበረተሰብ አቀፍ የጤና መልዕክተኞች (ጤኤሠ፣ ሞዴል ቤተሰቦችና ሌሎች)አቅማቸውን በሚከተሉት መንገዶች ያሳድጋሉ።

- ለጤኤሠ እና ለጤና ባለሙያዎች የአሠልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል። ለማአጤመ እና ሞዴል ቤተሰቦች በቁልፍ የቤት/የማህበረሰብ ተሞክሮዎች እና የሕፃን ማነቃቂያ ላይ ሥልጠና ይሰጣል።
- ለሕፃናት እንክብካቤ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይዘጋጃሉ፣ ይሰራጫሉ።

> ***መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፡-***
>
> - ▶ አመቻቾች ቁልፍ የቤትና የማህበረሰብ የሕፃናት እንክብካቤና ማነቃቂያ ላይ የአሠልጣኞች ሥልጠና ይወስዳሉ።
> - ▶ ዓመታዊ የትግበራ ዕቅድ ይዘጋጃል፤ እንዲሁም አጠቃላይ የሠለጠኑ አመቻቾች ቁጥር ይታወቃል።

### 4.2.10 የፕሮግራም ትግበራ ክትትል

- ቁልፍ የፕሮግራም አመልካቾች በወጥነት ይለያሉ።
- በሀገሪቷ የሚገኙ የሕፃናት እንክብካቤ ትግበራና ማነቃቂያ ፕሮግራም ለመከታተል የሚያስችል የመመዝገቢያና ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅና የድጋፍና ክትትል ሥርዓት ይዘጋጃል።
- ወሳኝ ባለድርሻዎችና አስተባባሪዎች የፕሮግራም ትግበራ ማስተካከያ ጉባዔዎችን በመደበኛ መልኩ ያካሂዳሉ።
- በሀገሪቱ የተሠራውን የጤናና ቀዳሚ ማነቃቂያ አገልግሎት ውጤትና ተፅዕኖ ዳሰሳ ለማድረግ መደበኛ ጥናት ይካሄዳል።

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦**

- በክፍል መገኘትን መከታተል።
- ወላጆች የሚሳተፉበትን ወይም የማይሳተፉበትን ምክንያት መለየት።

## 4.3 የቅድመ መደበኛ ትምህርት መመሪያ /ከ4-7 ዓመት/

### 4.3.1 ትኩረት የሚደረግባቸው ተጠቃሚ ክፍሎች

የቅድመ መደበኛ ትምህርት የሚያነጣጥረው ከ4-7 ዓመት ያሉ ልዩ ፍላጐት ያላቸውን ጨምሮ ሁሉንም ሕፃናት ማለትም ባህል፣ ፆታ፣ ማህበራዊ ደረጃና ዘር ሳይለይ የሚያካትት ነው።

**መሟላት ያለበት መሠረታዊ መስፈርት፦**

- ሕፃናቱ በእድሜ ከ4 ዓመት ያላነሱ ከ7 ዓመት ያልበለጡ መሆን አለባቸው።

### 4.3.2 የቅድመ መደበኛ ትምህርት የአካባቢና የቦታ ሁኔታ

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት አገልግሎት በማህበረሰብ አቀፍ፣ በግል፣ በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት፣ በእምነት ተቋማት በተቋቋሙ ቅድመ መደበኛ ት/ቤቶችና በሌሎች ወጭ ቆጣቢ መንገዶች በኩል ሊሰጥ ይችላል።
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት በቀልዘአት ማዕከላት፣ በማህበረሰብ መሰብሰቢያ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት መማሪያ ክፍል፣ ለሕፃናት ዕድገትና ትምህርት ምቹ በሆነ ቦታ ህጋዊ ፈቃድ ኖሮ ሊከናወን ይገባል።
- ማዕከሉ በቀላሉ የሚለይና የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል መሆኑን የሚያመለክት ግልፅ ምልክት የተደረገበት መሆን ይኖርበታል።
- አካባቢው ለሕፃናት ማራኪ፣ አስደሳችና ምቹ ቦታ ሊሆን ይገባል።
- የቦታው አቀማመጥ ለሕፃናትና ጐልማሶች ነፃ እንቅስቃሴ የሚያመች መሆን አለበት።
- ጥሩ ይዞታና ፅዳት ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው።
- መሠረታዊ የፅዳት መሣሪያዎች መኖር አለባቸው። ለምሳሌ መፀዳጃ ቤትና የእጅ መታጠቢያ ውሃ ሊኖሩት ይገባል።
- ክፍሉ በደንብ የተናፈሰ፤ በቂ የአየር ዝውውርና በቂ ስፋት ያለው መስኮት እንዲኖረው ያስፈልጋል።
- የሕፃናትን የፈጠራ ሥራ ለማስቀመጥ የሚያስችል ቦታ መኖር አለበት።

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች ፦**

- ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል ቢያንስ ከአካባቢው ቁሳቁሶችና ግብአቶች የተሰሩ መሠረታዊ ቁሳቁሶችን፣ የልጅ-ለ-ልጅ ማቴሪያሎችና እንደ እርሳስ፣ ወረቀት ወዘተ ሊኖሩት ይገባል።
- አንድ መምህርና ረዳቱ ባሉበት ክፍል ከ40 በላይ ሕፃናት አይመደቡም።

### 4.3.3 የቅድመ መደበኛ ትምህርት መማሪያ ማዕከል

- ቀላሉን ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የማሰብ ሂደቶች የሚያፋጥኑ/የሚያዳብሩ እንደ እንቆቅልሽ፣ የመገመት ጨዋታ፣ ታሪክና ተረት፣ የመሳሰሉ የተለያዩ አነቃቂ ጨዋታዎችና መሥሪያ ቁሳቁሶች መቅረብ አለባቸው።
- ፈጠራን ለማሳደግ በግድግዳው ላይ የሚታዩ ቀለማትና ቅርፃ ቅርፅ መኖር አለባቸው።
- የመማሪያ አካባቢው ተስማሚ ሆኖ በጐልማሶችና በሕፃናት መካከል ለሚኖረው መስተጋብር በቂ ዕድል የሚሰጥ መሆን አለበት።
- ለዳሰሳ ለፍተሻና ለሙከራ በቂ ዕድል ሊኖር ይገባል።

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦**

- ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል ሕፃናት እንዲማሩ፣ እንዲሮጡ፣ እንዲጫወቱ እና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችልና አጥር ያለው ሊሆን ይገባል።
- በክፍል ውስጥ/በበረንዳው ያለው ቦታ ለአንድ ሕፃን ቢያንስ አንድ ተኩል ካሬ ሜትር ሊኖረው ይገባል።
- የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ክፍል/ሕንፃ መስኮት ሊኖረው ይገባል።
- ንፁህ የመጠጥ ውኃ፣ የእጅ መታጠቢያ ቁሳቁስና አንድ መፀዳጃ ቤት ይኖረዋል።

### 4.3.4 ከቤት ውጭ የመጫወቻ መሣሪያዎች

ከቤት ውጭ መጫወቻ መሣሪያዎች፣

- በደንብ የተያዙ፣ ንፁህና ለዕድገት ተገቢ የሆኑ፣
- ለፈጠራና ለተለያዩ ክህሎቶች ዕድገት በቂ ዕድል የሚሠጡ፣
- አካባቢው አደጋን ለመከላከል በተገቢው መንገድ የተደራጀ መሆን አለበት።

**መሟላት ያለበት መሠረታዊ መስፈርት፦**

- ▶ የመወጣጫ መሰላልና ከአካባቢ ቁሣቁሶች የተሠሩ የዥዋዥዌ መጫወቻዎች ሊኖሩ ይገባል።

### 4.3.5 የቅድመ መደበኛ ሥርዓተ ትምህርት

- ጥቅም ላይ የሚውለው ሥርዓተ ትምህርት በተለያየ የዕድሜ ክልል ያሉ ሕፃናትን ሁለንተናዊ ፍላጐት መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ መሆን አለበት።
- በሁሉም ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት በመንግሥት የፀደቀው ሥርዓተ ትምህርት ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል።
- ሥርዓተ ትምህርቱ በአካባቢው ሁኔታ መሠረት ተደርጎ ይተገበራል።
- ሥርዓተ ትምህርቱ ለዕድገት ተገቢ የሆኑ ይዘቶችንና ተግባራትን ለመምራት የሚያግዝ ነው። ስለዚህ መምህራን የራሳቸውን ፈጠራ በመጨመር የሕፃናት ሁለንተናዊ ዕድገት ማፍጠን ይችላሉ።
- ሁሉም የሕፃናት ዕድገት ዘርፎች /ማህበራዊ ስሜታዊ፣ አካላዊ፣ አዕምሮአዊ ወዘተ. በቅድመ መደበኛ ት/ቤት ፕሮግራም እኩል ትኩረት ሊሠጣቸው ይገባል።
- ሥርዓተ ትምህርቱ ሕፃናት በማህበረሰቡ ውስጥ ውጤታማ ዜጎች እንዲሆኑ የሚያስችሏቸው ክህሎትን ለማዳበር መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል።
- ሁሉም የመማር ማስተማር ተግባራት ከፀደቀው ሥርዓተ ትምህርት ጋር የሚሄዱ መሆን አለባቸው።
- ሥርዓተ ትምህርቱ ለሁሉም መምህራን ሊሰጣቸው ይገባል።

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፦**

- ▶ መምህራኑ ሥርዓተ ትምህርቱን እንደ መመሪያ ይጠቀሙበታል
- ▶ መምህራን በአካባቢው ከሚገኙ ቁሣቁሶች የማስተማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁሶች ያዘጋጃሉ።

### 4.3.6 የቅድመ መደበኛ ትምህርት/ማዕከል ተግባራትን ማዋቀርና የጊዜ ሠሌዳ ማዘጋጀት

- በየቀኑ የሚከናወኑ ተግበራትን የሚያሳይ የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶ በክፍል ውስጥ መሰቀል አለበት።
- የየዕለቱ መርሃ ግብር የልጆችን ፍላጐት እንዲያሟላ ተደርጐ መስተካከል አለበት።
- ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት የሥራ ጊዜ ግማሽ ቀን ሆኖ ከ2፡00-6፡00 ሰዓት ከሰኞ እስከ አርብ ሥራ ላይ ይሆናሉ። ፕሮግራሙ ሙሉ ቀን ከሆነ ሕፃናቱ እረፍት የሚያደርጉበት ጊዜና ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል።
- ቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ዓመቱ በሦስት ወሰነ ትምህርት/ተርም/የተከፋፈለ ሆኖ በየ12 ሳምንቱ ከወላጅ ጋር የምክክር መድረክ ይኖራል።
- ከሰዓት በኋላ ለሚከናወን የድጋፍ ፕሮግራም ምንም ዓይነት የተለየ ክፍያ አይኖርም።
- በተለያየ ዕድሜ ክልል የሚገኙትን ሕፃናት ለማስተናገድ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችና እንቅስቃሴዎች ሊኖሩት ይገባል።
- ለጨዋታ፣ ሙከራና ፍተሻ እንዲሁም ለእረፍት በቂ ጊዜ ሊመደብ ይገባል።
- ሕፃናት በፈለጉት ጊዜ ወደ መፀዳጃ ቤት እንዲሄዱ ሊፈቀድላቸው ይገባል።

**መሟላት ያለበት መሠረታዊ መስፈርት ፦**

- ▶ መምህራን የሚሰጡትን ሳምንታዊና የዕለት ተዕለት ትምህርትን ከዓመታዊ የትምህርት መርሀ ግብር ያዘጋጃሉ።

### 4.3.7 መምህራንና ረዳት መምህራን

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት የሕፃናት ትምህርትና ዕድገት እንዲያግዙ ኃላፊነት የተጣለባቸው መምህራንና ረዳት መምህራን የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው፣

- ሁለንተናዊ የሕፃናት ዕድገት በሚመለከት ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው፣
- ከሕፃናት፣ ከወላጆችና ከሌሎች ጋር በቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል ውስጥ አብሮ የመሥራት ችሎታ ያዳበሩ፣
- የለጋ ሕፃናትን ዕድገት ለማሻሻል ቁርጠኝነት የሚያሳዩ፣
- ባህልን፣ ዘርን፣ የቤተሰብ እምነትንና ተግባራትን ወይም ሌሎች ልዩነቶችን ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ ሁሉንም ሕፃናት የሚወዱና የሚያከብሩ፣
- ስለ ሕፃናት መብትና ጥበቃ የሚቆሙ መሆን ይኖርባቸዋል።

<u>መምህራን፡-</u>

- መምህራን የ10 ወር የቅድመ መደበኛ ትምህርት ሥልጠና የምስክር ወረቀት ከመምህራን ትምህርት ተቋም መያዝ ወይም ክህሎታቸውንና እውቀታቸውን ለማሣደግ በተለይ በለጋ ሕፃናት አሳታፊ ትምህርት ላይ የ2 ወር ሥልጠና የወሰዱ ይሆናል።
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል ከፍተኛው የመምህር-ሕፃን ጥምርታ ከ4-5 ዕድሜ ክልል 1፥ 30፤እና ከ5-7 የዕድሜ ክልል 1፥40 ይሆናል።

<u>ረዳት መምህራን፣</u>

- ከመምህሩ/ሯ በተጨማሪ ረዳት መምህር ወይም ቀልዘአት ሞግዚት ለሁለቱም ቡድኖች /4-5 እና 5-7 ዕድሜ/ ይመደባል/ትመደባለች። ዋና መምህራንን ያግዛሉ።
- ጥሩ ዕውቀት ያላቸውና በወንጀል የማይጠረጠሩ መሆን አለባቸው።
- ቢያንስ 8ኛ ክፍል ያጠናቀቁ ሆነው በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መልዕክተኛነት ወይም በሌሎች ከቀልዘአት ጋር ተያያዥነት ባላቸው እንደቀዳሚ ማነቃቂያ በመሳሰሉ ርእሶች ሥልጠና የወሰዱ መሆን አለባቸው።

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፡-**

- የቅድመ መደበኛ መምህርት 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች ነው/ናት
- ተንከባካቢ ወይም ረዳት መምህር 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች ነው/ናት

### 4.3.8 የማስተማርና መማር ዘዴ

- የማስተማር ዘዴው፡- ሕፃን ተኮር ሆኖ ሕፃናቱ በመማር ሂደቱ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን አለባቸው።
- ቁሣቁስ፡- በተለያየ መንገድ ሕፃናት ሊጠቀሙባቸው የሚገቡ በቂ ቁሣቁሶች ይኖራሉ። መማር ሕፃናት በቀጥታ ከጎልማሶች፣ ከአከባቢና ከተለያዩ ቁሣቁሶች ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር የሚፈጠር ነው።
- መግጠምና መፍታት፡-ሕፃናት ቁሣቁሶችን የመዳሰስ፣ የመፍታት/የመግጠም፣ የመቀየር ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል።
- ምርጫ፡-ሕፃናት ምን መሥራት እንዳለባቸው እንዲመርጡ ነፃነት ሊሰጣቸው ይገባል። ሕፃናት የግል ፍላጐታቸውንና ግብን ተከትለው በመጫወቻ ቁሣቁሶች እንዲጫወቱ መደረግ አለባቸው።
- ቋንቋ፡- ሕፃናት ምን እየሠሩ እንደሆነ በቋንቋ ይገልፃሉ። በቋንቋ ሕፃናት በሚፈፅሟቸው ተግባራት ላይ አስተያየት ይሰጣሉ፣ ካላቸው ዕውቀት ጋር አዲስ ልምድ ያቀናጃሉ፣ ተባብረው ይሠራሉ።
- የጐልማሳ እገዛ፡-ጐልማሶች የሕፃናትን አስተሳሰብ፣ ፈጠራና ችግር መፍታት ጥረትን በተመለከተ እውቅና ይሰጣሉ፣ ያበረታታሉ።
- ማህበራዊ መስተጋብር፡-ሕፃናት ከአቻዎቻቸው ጋር የሚያደርጉት ማህበራዊ መስተጋብር ለመግባባትና ግኑኝነት ለመፍጠር ጠቃሚ ነው። ሕፃናት ከጓደኞቻቸው ሐሳብና እገዛ እንዲያገኙ፣ ለተሻለ ሐሳብ እገሌ ይሻላል እንዲሉ፣ በግልና በቡድን እንዲሰሩ ዕድል ይሰጣቸዋል።
- ተማሪ ተኮር አቀራረብ፡- ሕፃናት የጋራ ልምድ አላቸውና ልምድ መለዋወጥ ያስደስታቸዋል። ይህ ልምድ ልውውጥ ደግሞ ችግርን በጋራ የመፍታት ክህሎት እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል።

***መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፣***

- ሕፃን ተኮር መሠረት ያደረገ የመምህር-ሕፃን ግንኙነት።
- ለአሣታፊ ትምህርት አካባቢያዊ ቁሣቁሶች ከአካባቢው ይጠቀማሉ።

### 4.3.9 ጤናና አመጋገብ

- የጤና ሠራተኞች የሕፃናት ሁኔታን በተመለከተ መደበኛ ክትትል እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- መምህራን የሚጠቀሙባቸውን የዕድገት ክትትል ሰንጠረዦች ማቅረብ፣
- መምህራን ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ የመጀመሪያ እርዳታ መገልገያ ቁሳቁሶች እንዲኖሩ ማድረግ።
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት ከሕፃናት ጋር የሚሠሩ ሁሉም ሰዎች፣ ምግብ አቅራቢዎችን ጨምሮ፣
- ከተላላፊ በሽታ ነፃ መሆን አለባቸው፣ ይህ ከሁሉም ተላላፊ በሽታ ነፃ የመሆን ሁኔታ በሕክምና መረጋገጥ አለበት።
- ምግብ በሚዘጋጅባቸው ትም/ቤቶች/ማዕከላት ለሕፃናት የሚሰጡት ምግቦች አልሚና ተመጣጣኝ ይሆናሉ።
- ወላጆች ለሕፃናት ምግብ መቋጠር በሚፈቀድበት ቦታ አልሚና ተመጣጣኝ ምግብ እንዲቋጥሩ ይበረታታሉ።
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት የሚከናወነው አመጋገብ ጤናማና ንፁህ በሆነ አካባቢ መሆን አለበት።

**መሟላት ያለበት መሠረታዊ መስፈርት፡-**

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሁሉም ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት የዕድገትና የጤና ክትትል፣ ክትባትና የፀረ አንጀት ጥገኛ ትላትል ሕክምና እንዲሰጥ ያስተባብራል።

### 4.3.10 ከወላጆችና ከህብረተሰቡ ጋር አብሮ መሥራት

- ዓመቱን ሙሉ በወላጆችና መምህራን መካከል መግባባት እንዲኖር መልካም አጋጣሚ መፈጠር አለበት።
- የሕፃናትን መሻሻል በተመለከተ ወላጆችና/ተንከባካቢዎችና መምህራን መደበኛ በሆነ መልኩ መረጃ መለዋወጥ አለባቸው።
- በዓመት ውስጥ መደበኛ የወላጅ መምር ህብረት /ወመህ/ ስብሰባዎች ይካሄዳሉ።
- ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከሉን በተመለከተ ለሁሉም ወላጆች/ተንከባካቢዎች ግልፅና ሁሉን አቀፍ መረጃ መኖር አለበት።
- መምህራን በሕፃናት መኖሪያ ቤት አካባቢ ስላለው ሁኔታ መረጃ ማግኘት አለባቸው፣ በምስጢርም ይይዙታል/ለሌላ አሳልፈው አይሰጡም ከትምህርት ውጭ ለሆነ አላማም አይጠቀሙበትም።
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከሉ የተከናወኑ ድርጊቶች በወላጆች/ተንከባካቢዎች ቀን በዓመቱ መጨረሻ በሪፖርት ይቀርባሉ።
- ወላጆች ዕውቀታቸውን እንዲገነቡና አቅማቸውን እንዲያጠነክሩ የግንዛቤ ማዳበሪያ ዕድል ይሰጣቸዋል።
- ሕፃናት በማህበረሰቡ ተግባራት እንዲሳተፉ በቂ ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል።
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል ያሉ ተግባራትን ለማገዝ ከማህበረሰቡ ተወካዮችና ከወላጆች/ተንከባካቢዎች ጋር መተባበር ያስፈልጋል።
- የቅድመ መደበኛ ትም/ቤቱን/ማዕከሉ ሥራ ለመደገፍ የህብረተሰብ ተወካዮችና ወላጆች/ተንከባካቢዎች ግብአት የሚያቀርቡበት ሁኔታ መኖር አለበት።

**መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፡-**

- ▶ በቀን አንድ ጊዜ ልጆቻቸውን ሊያደርሱ ወይም ሊወስዱ የሚመጡ ወላጆች ከመምህራን ጋር ይገናኛሉ።
- ▶ ወላጆች በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት/ማዕከል ውስጥ በሚካሄደው የወላጆች ትምህርት ይሳተፋሉ።

### 4.3.11 ፍተሻ/Assessment/

- የሕፃናት ፍተሻ ሁሉን አቀፍና በሁለንተናዊ የሕፃናት የዕድገት ዘርፎች ላይ ያተኮረ መሆን አለበት።
- የሕፃናት ዕድገት ፍተሻ ተከታታይና ተገቢ ዘዴ የሚጠቀም መሆን አለበት።
- የፍተሻ ውጤቶች ክፍል ለመድገም ወይም ለመምረጥ አገልግሎት መዋል የለባቸውም።
- የሕፃናት የፍተሻ ውጤቶች ለወላጆች በተገቢው መንገድ መድረስ አለባቸው፣ ሕፃናትን በደረጃ ለመፈረጅ መጠቀም ግን ተገቢ አይደለም።
- ፍተሻ የሕፃናትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች የሚያሳይና የሚሻሽሉበት ሁኔታ የሚጠቁም መሆን አለበት።

| |
|---|
| **መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፡-**<br>▶ የሕፃናት ስም፣ የተወለዱበት ቀን፣ አድራሻና የልደት ሁኔታ መመዝገብ፣<br>▶ የምልከታ ዘዴን በመጠቀም ለእያንዳንዱ ሕፃን ተከታታይ ፍተሻ ማካሄድ። |

### 4.3.12 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል አስተዳደር

የአስተዳደር መዋቅሩ እንደሚከተለው ሊሆን ይገባል፣

- የትምህርት ሚኒስቴር የመሪነት ኃላፊነት ያለበት ሚኒስቴር ነው።
- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት የሚከናወኑትን የጤናና የምግብ ተግባራትን በተመለከተ ኃላፊነት አለበት።
- በክልል ደረጃ የክልል ትምህርትና ጤና ቢሮዎች፣
- በወረዳ የትምህርትና ጤና ጽ/ቤቶች፣ በቀበሌ ደግሞ የቀልዘአት ትግበራ ኮሚቴ ኃላፊነት አለባቸው።

| |
|---|
| **መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መስፈርቶች፡-**<br>▶ የሕፃናት ስም፣ የተወለዱበት ቀን፣ አድራሻና የልደት ሁኔታ መመዝገብ።<br>▶ የምልከታ ዘዴን በመጠቀም ለእያንዳንዱ ሕፃን ተከታታይ ፍተሻ ምዘና ማካሄድ። |

### 4.3.13 የፕሮግራም ውጤታማነት ክትትል

- ለቅድመ መደበኛ ትም/ቤት ውጤታማነት፣ የግብአት አጠቃቀምና አፈፃፀም መረጃ አስፈላጊ ነው።
- ስለ ሕፃናት፣ ስለመምህራን፣ ስለመሣሪያ፣ ወዘተ በተመለከተ የመነሻ መረጃ መያዝ ያስፈልጋል።
- መደበኛ በሆነ መልኩ በቅድመ መደበኛ ትም/ቤት ክትትል መካሄድ አለበት።
- የክፍል የተማሪዎች ውጤት ለወመህና ለትም/ቤቱ/ማዕከሉ ቦርድ ይደርሳል።
- መንግሥት መደበኛ የሆነ የክትትል ሥርዓት እንዲኖረው ያስፈልጋል።
- የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ለመቅረፅ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ባለሙያዎች ይመደባሉ።
- አመልካቾችና ትኩረት የሚሻው ግብ በግብረ ኃይሉ ይወሰናሉ፡፡

## 4.4 መደበኛ ላልሆነ መንገድ ለትምህርት ቤት ዝግጁነት መመሪያ

ለዚህ ፕሮግራም መስፈርቶች የግድ መጠቀም አያስፈልግም። ምክንያቱም ፕሮግራሙ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ባለው ሃብት መሠራት ያለበት ስለሆነ ነው።

### 4.4.1 በፕሮግራሙ የሚካተቱ ተጠቃሚዎች

- በህብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ ከ4-7 ዓመት ያሉ ሕፃናት ናቸው።

### 4.4.2 ፕሮግራሙ የሚተገበርበት መንገድ፣

- የልጅ-ለልጅ መተጋገዝ ፕሮግራም በመጠቀም ይሆናል።

### 4.4.3 በፕሮግራሙ የልጅ-ለ-ልጅ መተጋገዝ መሠረታዊ ነገሮች

- የልጅ-ለልጅ ፕሮግራም በተፈጥሮ የሚከሠቱ ሁኔታዎችን መሠረት ያደረገ ሆኖ ታላላቅ ሕፃናት ታናናሽ ወንድምና እህቶቻቸውን ለመንከባከብና ለመማማር እንዲችሉ ሁኔታዎች የሚመቻቹበት ዘዴ ነው።
- ታላላቅ ወንድምና እህቶች (አመቻቾች) ከታናናሽ እህትና ወንድሞቻቸውና ጐረቤቶቻቸው ጋር ይጫወታሉ።
- ከትምህርት ቢሮ በሚሰጡ መሠረታዊ ቁሣቁሶች፤ እንዲሁም ከአከባቢው የሚገኙ እንደ ጠጠር፣ አፈር፣ ባቄላ፣ ቅጠልና የመሳሰሉትን በመጠቀም ሊጫወቱና ሊማሩ ይችላሉ።
- ሕፃናት አመቻቾች ቢያንስ በሣምንት አንድ ጊዜ ከመምህራኖቻቸው አጭር ሥልጠና ያገኛሉ።
- ወጣት አመቻቾች ቢያንስ በሣምንት አንድ ጊዜ ከ3-5 ከሚሆኑ ዘመድ፣ ጐረቤት ጓደኛና ለቤታቸው ቅርብ ከሆኑ ሕፃናት ጋር ለአንድ ሰዓት ያህል ይጫወታሉ።
- ጨዋታ የመማሪያ መንገድ ነው። ለምሣሌ፣ ሕፃናት በጨዋታ ይቆጥራሉ፣ ቀለምና ፊደላት ይለያሉ፣ ተረቶች በመሳሰሉት መንገዶች ለመደበኛ ትምህርት ዝግጁ ይሆናሉ።

### 4.4.4 መደበኛ ባልሆነ ለትምህርት ዝግጁነት ይዘቶች

- አካላዊ እንቅስቃሴ ክህሎት የማዳበር ዕድል፣
- የግልና የቤተሰብ ኑሮ ክህሎት፣
- የፈጠራ መዳበር፣
- የአእምሮ ዕድገትን የሚያፈጥኑ ተግባራት፣
- እንደ ማንበብ፣ መፃፍ፣ ስሌት፣ ሒሳብ የመሳሰሉት መሠረታዊ ክህሎቶች
- የሥራ ግንዛቤና ችግር መፍታት ክህሎትን የሚያዳብሩ ተግባራት፣
- የማህበራዊ ችሎታና ተሳትፎ የሚያዳብሩ ተግባራት ያጠቃልላል።

### 4.4.5 ፕሮግራም ቀረፃና ተግባራዊ አደረጃጀት

- ለትም/ቤት ዝግጁነት ፕሮግራም ከ 4-7 ዓመት ዕድሜ ክልል ያሉ ሕፃናት የሚመለከት ነው።
- ወጣት አመቻቾች 5ኛ ወይም 6ኛ ክፍል ተማሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ።
- የአንደኛ እንዲሁም የ5ኛና 6ኛ ክፍል መምህራን ወጣት አመቻቾችን በማሠልጠንና በማስተባበር ሂደት ይሳተፋሉ።
- የአንደኛ ክፍል መምህራን ለፕሮግራሙ የተዘጋጁ ቁሣቁሶችን የክፍል ተግባራቸውን ለማሻሻል ሊጠቀሙ ይችላሉ።

ማቴሪያሎቹ እንዲጣጣሙ ተደርገው ወደ ተለያዩ የአካባቢ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል። ማቴሪያሎቹ የሚያጠቃልሉት የመምህሩ መምሪያ ለመምህራንና የአመቻች መምሪያ ለአመቻች ሕፃናት እንዲሁም ለተሣታፊ ህፃናት ፖኬጅ ነው። የሕፃናቱ ፖኬጅ የተረት መጽሐፍ፣ መጫዎቻዎች መዝሙሮችና፣ መልመጃዎች ወዘተ. ያካተተ ነው።

### 4.4.6 ቁጥጥርና ግምገማ

- የመነሻ ጥናት በማነፃፀርያና ሥራ በተጀመረባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለውን ልዩነት ለመወሰን አሁን ያለውን በወቅቱ መመዝገብና በትም/ቤት ዝግጁነት ያለውን ተፅዕኖ ማየት ያስፈልጋል።
- ግምገማው የፕሮግራሙ ማጠናቀቅን፣ በወቅቱ አንደኛ ክፍል መመዝገብንና ለትምህርት ዝግጁነትን መሠረት ያደረገና የፕሮግራሙ ውጤት፣ ያመጣውን ለውጥና ሂደት ላይ ያተኮረ ይሆናል።
- የልጅ-ለልጅ ትምህርት ልምድ ያላቸውና የሌላቸው ሕፃናት ለትም/ቤት ዝግጁነት ልዩነት እንዳለው ወይም እንደሌለው ይነፃፀራል።
- ግምገማው በተጨማሪም ፕሮግራሙ በወላጆች፣ በመምህራን በሕፃናት አመቻቾችና በህብረተሰቡ ላይ ያመጣው ለውጥ/ተፅዕኖ ይወስናል።